# በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ
# ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የሚመራው
# ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ

## የአዲስ አበባው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ ለበተነው የሐሰት ጽሑፍ የተሰጠ መልስ

«ደቂቀ እጓለ እመሕያው እስከ ማእዜኑ ታከብዱ ልበክሙ ፤ ለምንት ታፈቅሩ ከንቶ ወተሐሱ ሐሰተ ፤ አእምሩ ከመ ተሰብሐ እግዚአብሔር በጻድቁ»

እናንተ የሰው ልጆች ፥ እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ ? ከንቱ ነገርን ለምን ትወዳላችሁ ? ሐሰትንም ለምን ትሻላችሁ ? እግዚአብሔር በጻድቁ እንደ ተመሰገነ እወቁ ።

መዝ 4 ፥ 2-3 ።

ሚያዝያ 15/2005 ዓ/ም

ኖርዝ አሜሪካ

# <u>መግቢያ</u>

ቅዱስ ዳዊት እናንተ የሰው ልጆች እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ በማለት ለንስሐ ስፍራ ሳይኖራቸው ሐሰትን ፀንሰው አመፃን የወለዱትን ሰዎች የገሠጸበትን የቅዱስ መጽሐፍን ኃይለ ቃል መነሻችን ያደረግነው አለምክንያት አይደለም ። ሐሰትን እንደ ልብስ ለብሰው በልቡናቸው ሠራዒ መጋቢ ፈታሒ አምላክ የለም እንዳሉት የማኒ ልጆችና መሰሎቻቸው ፥ ፈራሽ በስባሽ የሆነውን የሰውን (የመንግሥትን) ኃይል ተገን አድርገው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሕገ ቀኖና ያፈረሱ ፣በአዲስ አበባ ያሉ ወንድሞቻችን ፥ ታሪክንና ሕዝብን ሳያፍሩ እናምነዋለን የሚሉትን እግዚአብሔርንም ሳይፈሩ ንስሐ በመግባት ፈንታ የሐሰት መጽሔት ጽፈው አውጥተዋል ። የሚገርመው መጽሔቱ የወጣው አባ ማትያስ ወያኔ ኢሕአዴግ መንበሩን በሰጣቸው ቀን መሆኑ ነው ። ያላስተዋሉት ነገር ግን ዛሬም እግዚአብሔር እነሱ በገፉአቸው በስደተኛውና በተሐራሚው የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ስደትና ሐዋርያዊ ተልእኮ መከበሩን አለማወቃቸው ነው ። ያን ለማስተዋል ቢታደሉ ኖሮ የቀደመውን ስሕተት በሌላ ስሕተት ለማረም ባልተነሡ ነበር።

መጽሔቱ ቤተ ክርስቲያናችን አንድ ትሁን ። ፓትርያርካችን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ናቸው እያለ ለጮኸው ሕዝበ ክርስቲያን የማጽናናት ቃልን የሚናገር አይደለም ።

መጽሔቱ በገዛ ሀገሩ ላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየታየና ዘሩ እየተጠየቀ ስለሚፈናቀለው ሕዝብ የሚያወራ አይደለም ።

መጽሔቱ «አማራንና የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አከርካሪ ሰብረናል» እያለ የሚደነፋውን ፣ ገና ከመነሻው በበረሃ የቀመመውን መርዝ የሚያመክን አይደለም ።

መጽሔቱ እየፈረሱ ስላሉት ገዳማቶቻችን ፥ በአስተማሪ እጦት እየተበተኑ ስላሉት የአብነት ትምህርት ቤቶች ፥ ቀዳሽ በማጣትና የማስቀደሻ ዕጣንና ዘቢብ በማጣት ስለሚዘጉ አብያተ ክርስቲያናት የሚናገር አይደለም ።

እነዚህ ልባቸውን እንደ ፈርዖን ያደነደኑ ወንድሞቻችን ያወጡት ሐሰተኛ መጽሔት በረኃብ ጽናት በየትምህርት ቤቱ ስለሚወድቁት ሕጻናት የሚናገር አይደለም ። ወይም ጊዜ አንሥቷቸው ዛሬ ከባዶ ባለሚሊዮን የሆኑት የገዢው ወርቅ ልጆች እንዴት ለደሃው ማሰብ እንዳቃታቸው የሚጠይቅ አይደለም ። ይህ ሁሉ አይደለም ።

ይልቁንም መጽሔቱ ላለፉት ሃያ ሁለት ዓመታት በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ካድሬዎች ሲደሰኩሩት የነበረውን የሐሰት ወሬዎች ከየትም ለቃቅሞ ያቀረበ ነው ። የስደተኛውና የተሐራሚው የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አባታዊ ፍቅር በሚሊዮን በሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ልጆች እንደ ገና መቀጣጠሉ እንቅልፍ የነሣቸው የገዢው ካድሬዎች ፥ የታላቁን አባታችንን ስም አጎደፍን ብለው የከተቡት ከንቱ ከታብ ነው ።

ከአገሪቱ ፕሬዝደንት ጀምሮ እስከ ቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር ድረስ ፥ ከሊቃነ ጳጳሳት ጀምሮ እስከ ቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ድረስ እውነቱን እየገለጹ ባሉበት ጊዜ ፥ ሐሰቱን እውነት እውነቱን ደግሞ ሐሰት በማለት ያቀናበሩት ቅንብር ነው። የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት «እናንተ የሰው ልጆች እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ ? ከንቱ ነገርን ለምን ትወዳላችሁ ? ሐሰትንስ ለምን ትሻላችሁ» ያለው በእርግጥ እንደነዚህ ያሉትን ነው ።

የክርስቶስ ገዳዮች የሐሰት ወሬ በከተማው እንዲወራ በማድረግ የክርስቶስን ትንሣኤ እውነተኛነት ለማስተባበል ብዙ ደክመው ነበር ። መቃብር ጠባቂዎቹም ጌታችን መነሣቱን ለአይሁድ ሲነግሯቸው እነዚሁ የክርስቶስ ገዳዮች ጠባቂዎቹን በገንዘብ ገዝተው የሐሰት ሥራቸው ተባባሪ ለማድረግ ሞክረው ነበር ። ይህንንም ወንጌላዊ እንዲህ በማለት ጽፎታል ። «ለጭፍሮቹ ብዙ ገንዘብ ሰጡአቸው ፡- እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ ። ይህም በገዡ ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ ስጋት እንድትኖሩ እናደርጋለን አሏቸው ። እነሱም (ጭፍሮቹ) ገንዘቡን ተቀብለው እንዳስተማሩአቸው አደረጉ ። ይህም እስከ ዛሬ በአይሁድ ዘንድ ይወራል» ብሏል ። ማቴ 28 ፥13-15 ።

አሁንም በዘመናችን ቅዱስ ፓትርያርኩን ከመንበራቸው ለማውረድ የአመፅ አስተባባሪዎች የነበሩት ፥ «ጭቁን ካህናት ነን»

በማለት ቤተ ክርስቲያንን ሰላም የነሡት እነዚህ ሰዎች ብኩርናውን ለመንግሥት አሳልፎ የሰጠውን የአዲስ አበባውን ኢሕጋዊ ሲኖዶስ ተጠቅመው የፈለጉትን ቢሉ አያስገርምም ። አሁን ሲኖዶሱን የሚያዙት ሰዎች የወያኔ ሰላዮች ሆነው ወያኔን መርተው አዲስ አበባ ሲያስገቡ በቅዱስ ፓትርያሪኩ ላይ ስም አጥፊ ጽሑፎችን ይበትኑ ነበር ። ዛሬም ያንኑ ነው እየሠሩ ያሉት ። ነገር ግን አይሁድ በገንዘብ የገዙት የወታደሮች የሐሰት ወሬ ቤተ ክርስቲያንን እንዳላሸነፋት ፥ የትንሣኤውንም እውነተኛነት እንዳልጋረደ ፥ የዘመናችን አሳዳጆች የሐሰት መልእክትም በሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ላይም ሆነ በሚመሩት ቅዱስ አባት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም ።

ታዲያ ታላቅ የታሪክ አደራ ያለበት ፥ ይህ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለዚህ የሐሰት ክስ መልስ በመስጠት ጊዜውን በከንቱ ለምን ያጠፋል ? የሚል ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው ። ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ይህንን መልስ የሚሰጥባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ።

1/ የሚመጣው ትውልድ አባቶቹና እናቶቹ ለቀኖና ቤተ ክርስቲያን መከበር ጊዜ ካነሣቸው ሐሳውያን ጋር ምን ያህል ተጋድሎ እንዳደረጉ እንዲገነዘብና ከየአቅጣጫው የሚመጡትን የሐሰተኞች ወንድሞችን የሐሰት ወሬ እንዳያደምጥ ለማስጠንቀቅ ።

2/ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎችም ይህ ዓይነቱ ስሕተት ወደ ፊትም እንዳይደገም የሚመጣውን ትውልድ ለማስተማር በእውነተኛዎቹ የታሪክ መዛግብት ላይ ተመሥርተው እንዲጽፉ የሚያስችል እውነተኛ መረጃ ለመስጠት ።

3/ ምንም እንኳ አብዛኛው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በአሁኑ ወቅት እውነቱን የተረዱ ቢሆንም ፥ በባለጊዜዎቹ ካድሬዎች የተበተነው የሐሰት መጽሐፍ አንዳንድ በቂ መረጃ ያላገኙ ወንድሞችንና እኅቶችን እንዳያሳስታቸው ለማድረግ ነው ።

በመሆኑም በሚቀጥሉት ገጾች በአዲስ አበባ ያለው ጊዜ ያነሣው የፖለቲካ ኃይል ሕገወጥ የፓትርያርክ ምርጫ አድርጎ በሐሰት መንበሩ ላይ ባስቀመጠበት ወቅት በመጽሔት አሳትሞ ለበተናቸው የሐሰት ጽሑፎች በዝርዝር መልስ እንሰጣለን ።

በመቀጠልም የአዲስ አበባው አካል የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ከዳር እስከ ዳር ያሰሙትን ጩኸት ወደ ጎን በማድረግና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመሻር ሐሰተኛ የፓትርያርክ ምርጫ አካሂዳለሁ ማለቱ እንደ ተሰማ በሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በሎስ አንጀለስ ከተማ ባደረገው አስቸኳይ ልዩ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ያወጣውን አጠቃላይ መግለጫ ሙሉ ቃል ፤ እንዲሁም በሐሰት ስለ ተሰየመው ሐሰተኛ ፓትርያርክ ከሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠውን መግለጫ እናቀርባለን ። እንዲሁም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን የሚመለከቱ ታሪካዊ ሰነዶች ለምስክርነት በዚህ ጽሑፍ ተካተዋል ።

## የአዲስ አበባው የሐሰት ጽሑፍ ዋና ዓላማ ምንድነው?

የአዲስ አበባዎቹ ወንድሞቻችን እንደ መልካም አዝማሪ በተቀዳሚነት ለማስደሰት የፈለጉት ፥ ጌቶቻቸውን በመሆኑ ፥ ከመጀመሪያው የጽሑፋቸው ዓላማ ያደረጉት፥ የብፁዓን አባቶቻችን ስደት ያለምክንያት የሆነ ስደት እንደ ሆነ ማሳየት ነው ። በመግቢያቸው ላይም ስለዚህ ሲናገሩ *«. . . ቤተ ክርስቲያን አስተምራ፥ መዓርግ ሰጥታ ፥ በረከቷን መግባና ተንከባክባ ያሳደገቻቸው ነበሩ ። ነገር ግን የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ሲሳናቸው የነካቸው ሳይኖር ሀገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን እየካዱ ወደ ውጭ ሀገር በመኮብለል የክህደት ተረከዛቸውን አነሡባት»* ብለዋል ። ጊዜ ያነሣው ታሪክ ሲጽፍ እንዲህ ነው ።

አገር የገደለ ፥ ትውልድ የበተነ ፥ አማራ ፥ ትግሬ ፥ ኦሮሞ እያለ በአንድነት የኖረውን ሕዝብ እርስ በርሱ ለማባላት እኩይ ምክር የመከረ ፥ ቂመኛና እኩይ ትውልድ *«የነካቸው ሳይኖር»* ብሎ ለመናገር ደፈረ ። ይህም ዋና ዓላማቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል ። ይኸውም በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ድርጅቶች በዓለም እጅግ አስከፊ ሬከርድ ያለው መንግሥት ፥ ጋዜጠኞቹን አስሮ ፥ እናትን ከልጅ ለይቶ ፥ ሕዝብን ከሕዝብ ፥ ሃይማኖት ከሃይማኖት የሚያነሣሣ መንግሥት ፥ ሕዝብን በዘርና በቋንቋ ለይቶ በገዛ ሀገሩ ስደተኛ የሚያደርግ መንግሥት ፥ የዲሞክራሲ መንግሥት እንደ ሆነ መስበክ ነው ። የአዲስ አበባዎቹ የሐሰት ምስክሮች የወያኔ ኢሕአዴግ ሰብአዊነት ካድሬዎች ናቸው ።

እነዚህ አባቶች የተሰደዱት አገሬ ፈረሰች ፥ ቤተ ክርስቲያኔ ተደፈረች ብለው ነው ። በእግዚአብሔር የማያምን ፥ ቤተ

ክርስቲያኒቱን ለማፈራረስ ከበረሃ ተማምሎ የመጣ የጎጥ ፓርቲ ቤተ ክርስቲያኒቱን ዙሪያዋን ከቦ አላሠራ ሲል ነው እነዚህ አባቶች ከሚወዷት አገራቸው የተሰደዱት ። የተሰደዱት አገራቸውን ከድተው ሳይሆን ፥ አገሩን የካደና ለአገር ታሪክ ክብር የሌለው የተወደደች አገራቸውን ስለ ወረረ በግዳጅ ነው ።

ከሁሉ የሚገርመው በመግቢያቸው ላይ የጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ነው ። ይህን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና የጠቀሱት በግፍ ከመንበራቸው ለተሰደዱት ቅዱስ ፓትርያርክና ቅዱስ ፓትርያርኩን ተከትለው ለተሰደዱ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ነው ። ይህም ጥቅስ አለቦታው የገባና አሁን በቤተ ክርስቲያኒቱ አዛዥ የሆነው አካል ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የማያውቅ በሕገ ፖለቲካ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራ አካል መሆኑን አመልካች ነው ። ቀኖናው *«አንድ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ጳጳስ መንበሩንና ሀገረ ስብከቱን ትቶ ወደ ሌላ ሀገረ ስብከት ይሄድ ዘንድ አይገባም. . . ኤጲስ ቆጶሳት ከሀገረ ስብከታቸው ወደ ሌላ ሀገረ ስብከት ቢሄዱ ከስድስት ወር የበለጠ አይኑሩ ። ሊቀ ጳጳሳቱ ሳይፈቅድላቸው ከዚህ የበለጠ ቢኖሩ ወይም ሀገረ ስብከታቸውን ትተው በሌላ ሀገር በዓለ ትንሣኤን ቢያከብሩ ከሹመታቸው ይሻሩ ይላል»*

የሚያስገርመው ይህን ቀኖና የሚጠቅሰው በመንበሩ ላይ ፓትርያርክ እያለ ፓትርያርክ አድርጎ በሕገ ወጥነት ያስቀመጣቸውን አባ ጳውሎስንና አባ ማትያስን መሪዎቼ በማለት የመረጠ አካል መሆኑ ነው ። ይህን ቀኖና ያፈረሱት እነዚህ ሰዎች ናቸውና ።

አባ ማትያስ በሊቀ ጵጵስና የሾሙአቸውን አባታቸውን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ክደው ፥ ሀገረ ስብከታቸውን ቅድስት አገር ኢየሩሳሌምንም ትተው ፥ ወደ ምዕራብ ሀገሮች በመኰብለላቸው ምክንያት በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የተወገዙና ስማቸውን ተቀምተው ሌላ ሊቀ ጳጳስ በስማቸው የተሾመባቸው ናቸው ።

አባ ጳውሎስ በትምህርት ሰበብ ወደ ውጭ መጥተው በዚያው ሲኖዶሳቸውን ከደውና በይፋ በሕግ ፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካል አይደለሁም በማለት ነበር ለረጅም ዘመን ያለ ሀገረ ስብከት በአሜሪካ የቆዩት ። ይህ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በአደባባይ ሊነበብ የሚገባው ለእነዚህ ነበር እንጂ በግፍ ለተሰደዱት ቅዱስ ፓትርያርክ እና ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አይደለም ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ግን በግፍ የተሰደዱ ናቸው ። በጠመንጃ አፈ ሙዝ የተሰደዱ ለመሆናቸው እርስ በርሱ የሚቃረነው መግለጫ ስለሚያስረዳን በቦታው እንተነትነዋለን ። ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትም ሕጋዊ ፓትርያርካቸው ከመንበራቸው ሲነሡ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሲሻር በወቅቱ «ሲኖዶሱ የወንበዴዎች ዋሻ ሁኗል» በማለት ተቃውመው ተሰድደዋል ። ይህን የስደታቸውን ታሪክም ደረጃ በደረጃ እናስቀምጠዋለን ።

## ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከኤጲስ ቆጶስነት እስከ ፓትርያርክነት

በቅድስት አገር ኢትዮጵያ ባሉ አባቶቻችን ስም በተጻፈውና የዘረኝነት መርዝ ባሰከራቸው የዘር ካድሬዎች የተበተነው መጽሐፈ ሐሰት የመጀመሪያ ክፍል አትኩሮት የሰጠበት ዋና ነገር ፣ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያን የቤተ ክርስቲያን አባትነት መካድና እግዚአብሔር ከወንድሞቻቸው መርጦ ለዚህ ታላቅ ክብር ያስቀመጠበትን መንገድ መቃወም ነው ። ይህን ዓላማቸውንም ለማሳካት ያለምንም ኀፍረት ቅዱስ ፓትርያርኩ የተመረጡበትን የቤተ ክርስቲያኒቱን የአገልግሎት ብቃት መመዘኛን ለመተቸት ሞክረዋል ። ይህን ሲሉ ግን ቅዱስነታቸው ተመርጠው ለዚያ ቦታ እንዳይበቁ የሚያደርግ ቀኖናዊ ምክንያት ለማቅረብ አልቻሉም ። እንደ ምክንያት ያቀረቡት የተመረጡት በመንግሥት ተጽዕኖ ነው የሚል ነው ። አንድ ፓትርያርክ ሲመረጥ ፥ መንግሥት በምርጫው ላይ ተጽዕኖ አሳድሮ የሚፈልገውን ያስመርጣል የሚለው አባባል ፣ እንኳን ከመንግሥት ጋር ታሪካዊ ግንኙነት ባላት ቤተ ክርስቲያን ቀርቶ ፥ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ምንም ግንኙነት የላቸውም በሚል የምዕራቡ አገርም ሳይቀር ሐሜት የሚያሳማ እንደ ሆነ ይታወቃል ። በመሠረቱ ሿሚዎቹ አሁን ሰማዕተ ሐሰት የሆኑትን ሁሉ ያጠቃልላል ። እውነተኞች ከሆኑ ለምን ያን ጊዜ ጥያቄ አላቀረቡም ። ሆኖም ግን አሁንም ይህን የሚሉት ሰዎች እነማን ናቸው ብለን ስንጠይቅ ፥ የወያኔ ኢሕአዴግን ሹማምንት ግራና ቀኝ አስቀምጠው ካህናቱን የሚያስፈራሩ ፥ ለእውነት ለመናገር ደፋር ያሉ ጳጳሳትን ቤታቸው ድረስ ገብተው የሚደበድቡ ፥ ባሕታውያንን በቤተ ክርስቲያን አውደ ምሕረት ላይ በጥይት የሚያስደበድቡ ናቸው ። በቅርቡ አደረግነው ባሉት የፓትርያርክ ምርጫ ላይም እንዴት በዓለም ሕዝብ ፊት ማፈሪያ እንደ ሆኑ ለማንም የተደበቀ ምሥጢር አልነበረም ። «እኛ ማዳመቂያ አንሆንም ። ምረጡ ከሚሉን የሚልኩትን ለምን በደብዳቤ አይሾሙልንም» ያሉት የዚያው

የአዲስ አበባው ኢሕጋዊ ሲኖዶስ አባላት ናቸው ፥ አዲስ አበባ ያሉት ሰዎች ። አባ ጳውሎስም ሆኑ ፥ አባ ማትያስ ሲመረጡ ፥ ከመንግሥት የጸጥታ ኃይላት ምን ያህል ወከባ ፥ ምን ያህል ማስፈራራት እንደ ነበረ በምርጫው የተሳተፉት ሁሉ ምስክር ናቸው ።

ለማንኛውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በመጀመሪያ ወደ ጵጵስና ፥ ከዚያ ወደ ፓትርያርክነት እንዴት መጡ ? የሚለውን ታሪካዊ እውነት ለአንባብያን ከዚህ እንደሚከተለው እናቀርባለን ።



ብፁዕ ቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት በ1971 ዓ ም አባ መርቆሬዎስ ተብለው በምሥራቅ ኢትዮጵያ ላለችው ለጎዴ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ ሆነው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተሾሙ ። ለዚህም ታላቅ ክብር የበቁት የቅድስና ሕይወታቸው ፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርትም ያላቸው ጥልቅ የሆነ ዕውቀታቸው ታውቆ ነው ። አሁንም ቢሆን ከዳር እስከ ዳር በመላው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ዘንድ ሁሌ እንዲናፈቁ የሚያደርጋቸው ይህ ታላቅ የሆነው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርትና አገልግሎት ያላቸው ፍቅር ነው ።

በጎዴ በኤጲስ ቆጶስነት ተመደበው ሲሠሩ ትልቅ የሥራ ውጤት ያስመዘገቡ በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድም የተወደደዱ አባት ሆነው ሐዋርያዊ ተልኮአቸውንና የቤተ ክርስቲያናቸውን አደራ ተወጥተዋል።

ከዚያም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ውሳኔ ወደ ጎንደር ሀገረ ሰብከት ተዛውረው ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነዋል ። የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከሆኑበትም ጊዜ ጀምሮ ባስመዘገቡት የሥራ ብቃት አምስት ጊዜ በብሔራዊ ደረጃ በተከታታይ በአንደኛ ደረጃ ተሸልመዋል ። ራሳቸው ቤተ ክርስቲያናችን ካፈራቻቸው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ለዚያውም ታላቅ ጥረትና ትዕግሥት የሚጠይቀው የድጓ መምህር በመሆናቸው ፥ በየቦታው ወድቀው ያለ

ደጋፊ ያሉትን የአብነት መምህራን ያስታወሱና ከፍተኛ የሆነ የአብነት ትምህርት ቤት እንዲስፋፋ ያደረጉ ናቸው። በመሆኑም በየክፍለ ሀገሩ ያሉ የአብነት መምህራን ከሁለት መቶ ብር በላይ የወር ደመወዝ እንዲያገኙ በማድረግ የሊቃውንቱን ሕይወት አበርትተዋል ፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችና የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ ፣ የአራቱ ጉባኤ መምህራንና ተማሪዎች በቂ ቀለብ እንዲያገኙ አድርገዋል ። ለዚህም ቤተ ክርስቲያን ምስክር ናት ።

እነዚህ አባታቸውን አሳፋሪ ፥ አገራቸውን ደፋሪ የሆኑ ሰዎች ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን የቀይ ሽብር አስፈጻሚ በማስመሰል እንደ አንድ ክስ አቅርበዋል ። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በቀይ ሽብር ወቅት የት እንደ ነበሩ እነዚህ የትውልድ ማፈሪያዎች ሳያውቁ ቀርተው አይደለም ። ቀይ ሽብር የተባለው አሳዛኝ የጭንቅ ወቅት የነበረው ከ1968-1969 ዓ. ም. ነበር ። በዚያ ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ ገና በአዲስ አበባ ከተማ የብሥራተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አለቃ ነበሩ ። ከላይ እንደጠቀስነው የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው የተመደቡት በ1972 ዓ.ም ሲሆን ፥ የተመደቡትም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ነበር እንጂ በሌላ በማንም አልነበረም ።

ማንም እንደሚያውቀው ጎንደር የዜማ እና የመጻሕፍት ትምህርት ቤቶች የማስመረቂያ ቦታ ናት ። በዚህ ምክንያት በከተማዋ ቤት ንብረት መሥርቶ ከሚኖረው ይልቅ በትምህርት የሚኖረው የሊቃውንት ቍጥር ይበልጣል ። ከዚህም የተነሣ በጎንደር የሚማሩና የሚያስምሩ መምህራንና ተማሪዎች የቀለብ ችግር ሲገጥማቸው እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሁለትና ከሁለት በላይ ተማሪ በመደበኛነት እያገለገለ ቀለብ እንዲያገኝ በማድረግ ለዘመናት ጎልቶ ይታይ የነበረውን ችግር ለማቃለል ጥረት አድርገዋል ።

የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በነበሩ ጊዜ ሐዋርያዊ ተልእኮን በማፋጠን ፥ መጻሕፍትን በማሰራጨት ፥ ሰበካ ጉባኤን በማጠናከር እንደዚሁም ሕዝቡን በሚያሳትፍ የልማት ሥራ እንቅስቃሴ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ዋና ተጠቃሽ በመሆናቸው የእርሳቸው ሀገረ ስብከት ሁል ጊዜ በዋናነት የሚጠቀስ ነበር ። በተከታታይ ከሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት እየተመረጡ ለሽልማት ያበቃቸው የነበረውም ይህ ትጋታቸውና ለቤተ ክርስቲያን ያላቸው ቀናዒነት ነበር ።

«ዘመን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል» እንዲሉ ባለዘመን ሆነው ቅዱስነታቸውን ከመንበራቸው አሳደው ቤተ ክርስቲያኒቱን በኃይል የያዙ ወገኖች ፣ ይህን የቅዱስ ፓትርያርኩን የአገልግሎት ታሪክ የሚያስተባብል መረጃ አላቀረቡም ። ምክንያቱም ይህ የቅዱስ ፓትርያርክ ታሪክ በብልሃት የተፈጠረ ሳይሆን በተግባር የተፈተነ የሥራ ፍሬ በመሆኑ ነው ። በመጀመሪያዎቹ የሊቀ ጵጵስና አገልግሎት ዘመናቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ የሽልማት ኮሚቴ የቀረበውን የሥራ ሪፖርት አጥንቶ በሚዛን ላይ አስቀምጦ ይህን የሥራ የሽልማቱ አሸናፊ ይሆናል ባለው መሠረት ነው አሸንፈው ለአምስት ጊዜ ያለማቋረጥ በተከታታይ የተሸለሙት ። ይህ እንግዲህ ሥራን በተመለከተ ነው ።

የሥራ ብቃትን ሀገራዊ ከሆነው ሊቅነት ጋር አስማምተው የያዙ አባት ፓትርያርክ መሆን አልነበረባቸውም ካሉ ፥ ለመሆኑ መመዘኛው ምን መሆን ነበረበት ? እንደ ዛሬው ጊዜ ፓትርያርክ ለመሆን መመዘኛው ከፖለቲካ መሪዎች ጎጥ መወለድና በእነሱ ቋንቋ መናገር አልነበረምና ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ሲመደቡ ሀገረ ስብከቱ ቢሮ አልነበረውም ። የሊቀ ጳጳሱ መኖሪያ አርጅቶ ወዳድቆ ነበር ። በሊቀ ጵጵስና ዘመናቸው የመንበረ ጵጵስናውን ሕንጻ ከማሳደሳቸውም በላይ ከአሥራ አምስት በላይ ክፍሎችና አንድ ሁለ ገብ አዳራሽ የሚያጠቃልሉ ሕንጻዎች አስገንብተው መንበረ ጵጵስናው በክፍለ ሀገሩ ከሚገኙት የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በላይ ደረጃ እንዲኖረው አድርገዋል ። በወቅቱ እንዲህ ያለ የተሟላ መንፈሳዊ አስተዳደር ያለው ሀገረ ስብከት ስላልነበረ የእርሳቸው ሥራ በታላቅ አክብሮት ይነሣ ነበር ። በሀገረ ስብከቱ ያሉት አገልጋዮች ተግቶ ለሥራ የሚያተጋ ታላቅ እረኛ በማግኘታቸው ፥ ታላላቆቹ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እና መምህራን ደግሞ ለዘመናት ተረስተውበት ከነበሩበት ያስታወሳቸውና ቀዋሚ ደመወዝ የመደበ ሊቀ ጳጳስ በማግኘታቸው እጅግ ደስተኞች ነበሩ ። በዚያ ወቅት ይህ ዓይነት እንቅስቃሴ የነበረው ሀገረ ስብከት የትኛው ነው ? የሠራተኛ ደመወዝ ያሻሻለ ፥ለአብነት መምህራን ደመወዝ የመደበ ፥ አሥር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተሟላ የመንበረ ጵጵስና የገነባ ፥ በደን ልማት በእርዳታ ማስተባባሪያና በተግባረ እድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያሳየ ማንነው ? ይህ ሁሉ የሥራ ብቃትስ የት ሂዶ ነው ደርግ መደባቸው የሚባለው ? ይህ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ማሻሻል የት ሂዶ ነው በሌላ ተደግፈው ነው የተመረጡት የሚባለው ?

ያን ጊዜ ፓትርያርክ ሆኖ ለመመረጥ የዘር ፖለቲካ እንደ አሁኑ የለም ነበር ። ያን ጊዜ የሙስና ማዕበል እንዳሁኑ ቤተ ክርስቲያንን አላናጋትም ነበር ። ያን ጊዜ እንደ አሁኑ ለጵጵስና ከሁለት አስከ አምስት መቶ ሺህ ብር ፤ ለደብር ልቅና ከመቶ እስከ መቶ ሃምሳ ሺህ ጉቦ የሚጠየቅበት መንበረ ፓትርያርክ ቤተ ክርስቲያን አልነበራትም ። አባቶቻችን ጸጋ እግዚአብሔርን በገንዘብ የሚሸጡ አልነበሩም ። ተሿሚዎቹም እንደ ስምዖን መሠርይ በገንዘብ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመግዛት አይከጅሉም ነበር ። ያን ጊዜ ይነስም ይብዛም የሚያዋጣው ሥራ ነበር ። ተሿሚዎቹም መንፈሳውያን ፥ በዕድሜና በትምህርት የከበሩ አባቶች ነበሩ ። ለዚህ ነው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የተሾሙት ።

በዚያ ጊዜ አገራችን የእርስ በርስ ጦርነት ላይ በነበረችበት ወቅት ሰላማዊ መንገድ ለመፈለግ ከየክፍለ ሀገሩ በሽንጎነት የተወከሉትን ፥ ለዚያውም የጊዜው ገዢ ፓርቲ ያይደሉትን ፥ ለመኮነኛ የፓርቲ አባል ነበሩ ብለዋል ። የዚያን ጊዜውስ ሀገርን ይዞ የተነሣ ነበር ። የአሁኑን የዘረኝነት ፓርቲ አባላትን ምን ሊሉአቸው ይሆን ።

በቅርቡ የሞቱት አባ ጳውሎስ የሹመታቸው መጽደቂያ ቀን እንዲህ ብለው ነበር *"ከዚህ ቀን ለመድረስ ብዙ መሥዋዕትነት ተከፍሏል ፣ ትግሉ የጠየቀው በአገር ውስጥ ብቻ አልነበረም ሁሉም በአለበት ሆኖ ታግሏል ። ማንም የትም ሆኖ አገሩን የረሳ የለም የተሰደዱት ካልተሰደዱት የታሠሩት ካልታሰሩት እኩል ተሰቃይተዋል ነጻነታቸውን ላለማስደፈር መሥዋዕትነት ከፍለዋል"* ... እነዚህንስ ማን ሾማቸው ይባል ይሆን ? በእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የሚመራ አካል ሌላውን በሰው ድጋፍ ተሾሙ ብሎ ከባለ ሥልጣን ጋር የሚያሳይ ፎቶ እያሳዩ ተጠያቂ ማድረግ ምን ይሉታል ?

ከላይ እንዳመለከትነው ፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ መጀመሪያ ወደ ጵጵስና የመጡት ፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ተመርጠው ፥ ለዘመናት በክብር የኖረውን ታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን ዜማ የድጓ መምህር መሆናቸው ታውቆ ፥ ከደጋጎቹ አባቶች ተመርጠው ነው ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ለታላቂቱ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለመሆን የበቁት ፥ በመንበሩ ያሉትን ተጋፍተው ፥ የዘመኑን ጠመንጃ አንጋቾች ተሰፋ አድርገው አይደለም ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በማረፋቸው ቤተ ክርስቲያን መሪዋን ሕጋዊ በሆነ መንገድ በመረጠችበት ወቅት ነው ። የተሾሙትም በሊቀ ጵጵስናቸው ዘመን አድናቆትን በማትረፋቸው በወንድሞቻቸው በሊቃነ ጳጳሳት ፥ በገዳማት አበ ምኔቶችና በካህናት እንዲሁም በምእመናን ተመርጠው ነው ። በመሆኑም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ናቸው ።

## <u>ብፁዕ ወቅዱስ ከመንበራቸው ከመሰደዳቸው በፊት ምን ሠሩ ?</u>

የአዲስ አበባዎቹ ወገኖቻችን ፥ ወያኔ ኢሕአዴግ ገና በረሃ እያለ ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠላት እንደ ሆነች በሚያውጅበት ጊዜ ቅዱስ ፓትርያርኩን ይከሳቸው በነበረው ዘረኛ ክሱ ላይ ተመሥርተው ያን እንደ ገና ሲያላዝኑ መገኘታቸው የሚያስገርም ነው ። ወያኔ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በጠላትነት ለማጥፋት በዕቅድና በዓላማ እንደ ተነሣ ለማወቅ ዛሬ ዛሬ መሥራች አባላቱ የሆኑት እያወጡአቸው ያሉትን ታሪካዊ ሰነዶች መመልከት ነው ። ወገኖቻቸውን በረኃብ አለንጋ እንደ ቅጠል እንዲረግፉ እያደረጉ ፥ ለረኃብተኛ የተሰጣቸውን እህል መሣሪያ ይገዙበት የነበሩት ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን በኃይል ይዘው ሊከሷት ይሞክራሉ ። እነርሱ የዘነጉት ቢሆንም ታሪክ የማይረሳውን የቅዱስ ፓትርያርኩን ተግባር እናስታውሳቸው ።

### <u>1/ ቅዱስ ፓትርያርኩ በዚያ አስቸጋሪ ወቅት የቤተ ክርስቲያን ሕልውና እንዳይናጋ የጠበቁ አባት ናቸው ።</u>

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ሆነው የተሾሙበት ወቅት አገራችን ታላቅ ፈተና ላይ የነበረችበት ወቅት ነው ። በአንድ በኩል አገሪቱን የሚመራው መንግሥት የሚከተለው ርእዮተ ዓለም እግዚአብሔር የለሽ መሆኑ ቤተ ክርስቲያን ራሷን በራሷ እንድትደግፍ ግድ ብሎአት ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ ኤርትራን በማስገንጠል መርዝ የሆነውን የዘረኝነት ተንኮላቸውን በኢትዮጵያ ላይ ሊነሰንሱ የተዘጋጁት ፥ ታላላቆቹን የትግራይ ገዳማትና አድባራት የጦርነት ቀጠና በማድረጋቸው ፥ ምእመናንና ካህናት ከባድ አደጋ ላይ ነበሩ ። በዚህ ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያን ራሷን በራሷ የምትችልበትን መንገድ በከፍተኛ ደረጃ እንድታስብበት ፥ ካህናቱም ከመንፈሳዊው አገልግሎት ጎን ለጎን በተለያዩ የሙያ ሥራዎች አገራቸውን የሚጠቅሙበትን ልምድ እንዲቀስሙ ፥ ባለፉት ቅዱሳን አባቶች የተጀመረው የሰበካ ጉባኤ ማደራጀትና የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ እንቅስቃሴ በሰፊው እንዲከናወን አድርገዋል ።

ሰኔ 29ቀን 1982 ዓ.ም.

ለአቶ መለስ ዜናዊ
ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ
ዋና ጸሐፊ።

ጉዳዩ፤ <u>በኢትዮጵያ የሃይማኖት መሪዎች የወጣ የጋራ የሰላም ጥሪን ስለማስተላለፍ</u>

ሀገርን የሚያፈርስ ሕዝብን የሚበታትን ጦርነት ተወግዶ በምትኩ ሰላምና ደኅንነት እንዲሰፍን እኛ የሃይማኖት መሪዎችና መላው ምዕመናን ያልተቋረጠ ጸሎት ስናደርግ ቆይተናል፤ እያደረግንም ነው።

በተለይም በሰሜኑ ያገራችን ክፍል ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ መጥቶ በአሁኑ ወቅት ከመቼውም ጊዜ ይልቅ እጅግ አስከፊ በሆነ ደረጃ ላይ የሚገኘው ጦርነት እንዲቆም፤ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የሰላም ውይይቶች እስከዛሬ ድረስ የታሰበውን ያህል አንዳችም መልካም ውጤት ለማስገኘት አለመቻላቸው እጅግ አሳስቦናል። የሕፃናት ዕልቂት፤ የቤት ንብረት መፍረስ፤ የብዙ ሺህ ሰላማዊ ሕዝብ ሕይወት ማለፍ፤ የልማት አውታሮች መፈራረስ፤ በየቦታው የሕዝብ ፍርሃትና ሥጋት እጅግ አስጨንቆናል።

ከዚህም የተነሳ ሰኔ 27ቀን 1982 ዓ.ም. የጋራ ስብሰባ አድርገን ያወጣነውን የሰላም ጥሪ /አንድ ገጽ/ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን እየላክን፤ ጥሪያችንን ተቀብላችሁ በየደረጃውም በምናደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ በጉልህ በመሳተፍ ያልተቋረጠ ድጋፍና ትብብር እንድታሳዩን ከጥብቅ አደራ ጭምር በሁላችንም ፈጣሪ ስም እንጠይቃለን።

የምትሰጡንንም መልስ ባስቸኳይ እንጠባበቃለን።

የሁላችንም ፈጣሪ በሀገራችን ሠላምን ይስጠን።

አባ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርእሰ
ሊቃነ ጳጳሳት
ዘኢትዮጵያ

ሐጂ ዑመር ሑሰይን ዓብዱልዋሒድ
የኢትዮጵያ የእስልምና
ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ
ሊቀ መንበር

አባ ጳውሎስ ፃድዋ
ካርዲናል ሊቀ ጳጳሳት
ዘካቶሊካውያን

ቄስ ፍራንሲስ እስጢፋኖስ
የኢትዮጵያ ወንጌላዊት
ቤተክርስቲያን መካነ
ኢየሱስ ፕሬዚዳንት

## 2/ በጦርነት የሚፈሰውን ደም ለማስቆም የሰላም ጥረት አድርገዋል ፡፡

ቅዱስ ፓትርያርኩ በዚህ ሳይወሰኑ በመንግሥትና በወያኔ ኢሃዲግ መከካከል ይካሄድ የነበረውን ጦርነት በሰላም እንዲቋጭ ለማድረግ ጥረት አድርገው ነበር ፡፡ ይኸውም በሀገር ውስጥ ያሉትን የሃማኖት መሪዎችን በማስተባበር የሰላም ጥሪ ለሁለቱም አካላት አቅርበው ነበር ፡፡ ለመንግሥት ራሳቸው በአካል ተገኝተው የሰላሙን መልእክት ያቀረቡ ሲሆን በበርሃ ለነበረው ጦረኛ ኃይል ግን በዓለም ዓብያተ ክርስቲያናት ተወካይ በኩል እንዲደርስ አድርገው ነበር ፡፡ (መረጃውን በገፅ 9 ይመልከቱ)

## 3) በረሃብና በጦርነት የተጎዱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲረዱ አድርገዋል ፡፡

የዛሬዎቹ ባለጊዜዎች የበሉበትን ወጪት ይሰበሩት እንጂ ብፁዕ ወቅዱስ ትግሬ ፥ አማራ ፥ እገሌ እያሉ የከፋፈሉ አልነበሩም፡፡ ታላላቆቹ የትግራይ አድባራት እንዲሁም ሃይማኖተ ጽኑ የሆነው የትግራይ ሕዝብ በችግር ላይ ባለበት ወቅት ቤተ ክርስቲያን የበኩሏን እርዳታ እንድታደርግ መመሪያ ሰጥተዋል ፡፡ ለዚህም በዚያ ወቅት የልማት ኮሚሽኑን ይመሩት የነበሩ አባ ጢሞቴዎስ ካልዘነጉት ወይም በስተርጅናቸው የራሳቸውን የሥራ ውጤት ካልካዱት የሚመሰክሩት እውነት ነው ፡፡ በሰሜኑ በኩል የነበረው የእርስ በርስ ጦርነት ሕዝቡን ከባድ ችግር ላይ ሲጥል ካህናቱና ገዳማቱ ከዚያ አላመለጡም ፡፡ ብፁዕ ወቅዱስም ማድረግ በሚችሉበት አቅም ሁሉ እነዚያን ታላላቅ ገዳማት አልረሱም ነበር ፡፡ ለምሳሌ የታላቂቱ ገዳም የአኵሱም ጽዮን ካህናት እጅግ ከባድ ችግር ላይ ባሉበት ወቅት ፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድሳት በሚል ስም ለካህናቱ እገዛ እንዲውል ከመቶ ሺ ብር በላይ እንዲሰጥ አድርገዋል ፡፡ በዚህም በወቅቱ ከነበረው መንግሥት ጋር ለማጋጨት፥ «ገንዘቡን የላኩት ለአኵሱም ጽዮን ሳይሆን ለወያኔ ነው» በሚል ያሳበቁት ፥ ዛሬ እንደ ገና አዲስ መልክ ይዘው የተነሡት ከሳሾች ናቸው ፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በመንበራቸው የቆዩት ለሦስት ዓመታት ነው ፡፡ በዚህ ወቅት የለበሱትን ልብስ እንኳ ያልቀየሩ አባት ናቸው ፡፡ እኒህን አባት «የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብ ያለአግባብ አባክነዋል» በማለት የሚከሱት ደግሞ ላለፉት ሃያ ሁለት ዓመታት ቤተ ክርስቲያኒቱን የደም እንባ እንድታለቅስ ያደረጉ ናቸው ፡፡

ስለዚህ አካል ምን ማለት ይቻላል ? ልብስ በመቀያየር ሱስ በዓለም ኦርቶዶክሳውያን መቀለጃና መተረቻ የሆነው ማነው ? ራስን ለማምለኪያ ፎቶ ለመለጠፍና ሐውልት ለመትከል የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት እንዲወጣ ያደረገው ማነው? የቤተ ክርስቲያኒቱ ካዝና የመንግሥት ካዝና እንዲሆን ያደረገው ማነው ?

እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በአዲስ አበባ ያሉት ወገኖች አይመልሷቸውም ፡፡ ዛሬ የቤተ ክርስቲያኒቱን አደባባይ ይዘው የቤተ ክርስቲያን አንደበት የሆኑት ሰዎች ፥ ቀድሞ ቀሚስ ለብሰው መስቀል ጨብጠው የዘረኛው ፓርቲ አባላትና ሰላዮች የነበሩ አሁን ደግሞ ጭራሽ የባሰባቸው ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለግል ጥማታቸው ማርኪያ ያደረጉ፡ በጉቦና በብልግና ያረከሱዋትም እነሱ ናቸውና ከነእሱ ሌላ አንጠብቅም፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብ የማይረሳውን እውነታ ለማስታወስ እንዲህ እንላቸዋለን ፡፡

«እናንት የማታፍሩ! በቤተ ክርስቲያን አውደ ምሕረት ፓትርያርክ ብላችሁ በመደባችኋቸው ሰው አንጋቾች የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጅ በሽጉጥ ግንበሩን ተመትቶ ሲገደል የት ነበራችሁ ? የጎንደር ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን አጸድ አምልኮተ እግዚአብሔርን መፈጸሙ ወንጀል ሆኖበት በመትረየስ መታጨዱን እንዴት ረሳችሁት? በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ዘመን ተከብሮ በኖረው የጳጳሳት መኖሮያ ቤት እየገቡ በቆመጥ የቀጠቀጧችሁ ማን ናቸው ? አቡነ መርቆሬዎስ ናቸውን?

የመማፀኛ ከተማ ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን የተጠለሉ ወጣቶችን በፖሊስ አስደብድበው ወደ እስር እንዲላኩ ያደረጉ ፥ በአንድ ቀን በአዲስ አበባ ብቻ በሺዎች የሚቈጠሩ ልጆች ግንቦት ሰባት ቀን ሲገደሉ *«ልጆቻችሁ አርፈው እንዲቀመጡ ምከሩዋቸው»* በማለት ልጅ አልባ በሆኑት እናቶች ላይ ያላገጡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ናቸውን ? ለሞተው ልጃቸው ማልቀስ ወንጀል ሆኖ እናቶች እስር ቤት እንዲወረወሩ ያደረጉ ማን ናቸው ? አማራ ነፍጠኛ ፥ አማራ ምን ሊያደርግ መጣ እያስባሉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን እምነት ተከታይ በሙሉ በመላው ኢትዮጵያ እምነቱን እንዳያከናውን ያደረጉ እነማን ናቸው ? ይህ ታሪካችሁ ነው ? ይልቁንስ ልባችሁን ማደንደኑን ትታችሁ የሃያዎቹን የቤተ ክርቲያን የመከራ ዓመታት ተመልከቱት ? ነቢዩ እንዳለው «ከንቱ ነገርን ለምን ትወድዳላችሁ ? ሐሰትንም ለምን ትሻላችሁ »?

እነ አባ ጢሞቴዎስ «ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እዲህ ዓይነት ብልሽት የታየበት አሰተዳደር የለም» በማልት የተናገሩት «ቤተ ክህነቱ ተመዝብሯል ይመርምር» ያሉት ዛሬ ቃላቸውን ካልለወጡት ያን በማየት አልነበረምን ? እነ አባ ገብርኤል በዓለም አደባባይ ያን ሁሉ የክስ ዝርዝር ያቀረቡት በቅርብ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከባድ ችግር በማየት አልነበረምን ? እነ አባ ማትያስ ዛሬ ሁሉን ለመካድ

የበቁበት ፥ የቀድሞውን አባ ጳውሎስን ይከሱበት የነበረበት ንግግራቸው መነሻ ምን ነበረ ? ይደረግ የነበረው ከመንፈሳዊነት የራቀ መሆኑን በማወቅ ሕሊናቸው መስከርባቸው አልነበረምን ?

በአዲስ አበባ ያሉት ወገኖቻችን ፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከቀድሞው የኢትዮጵያ ርእሰ ብሔር ጋር ፎቶ መነሣታቸውን እንደ ትልቅ ወንጀል አቅርበዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በወቅቱ የነበረውን መንግሥትና ፥ በበረሃ የነበረውን ኃይል ለማስታረቅ የሰላም ኮሚቴ አቋቁመው ለአገሪቱ ሰላምና አንድነት ከፍተኛ ጥረት አድርገው ነበር ።

እነ ዓባይ ፀሐዬን እየጠሩ ማስፈራሪያ ማድረጉን ፥ ቤት ድረስ መጥቶ በዱላ ጳጳሳትን መቀጥቀጡን ፥ ምን እንደሚሉት አናውቅም ። በወቅቱ ሀገሪቱን ከሚመሩት ባለሥልጣን ጋር መገናኘታቸው ያስገርማልን ? የትሕትና አባት እንደ መሆናቸው በአክብሮት ሰላምታ መስጠታቸው ያስነቅፋልን ? ታሪክ እንደሚያስተምረን ብዙ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ አገሮች በኮሚንስት መሪዎች ሥር ነበሩ ፣ ከእነሱም ጋር ብዙ ነገር አሳልፈዋል ። ቅዱስ ፓትርያርኩ የማያምንን ሰው ግድ መስቀል ካልተሳለምክ ብለው መጋጨት ወይም አክብሮት መንሣት ነበረባቸው በሚል አስተሳሰብ የተሰነዘረ ከሆነ አለማስተዋል ነው ። አንድ የአገር መሪ ክርስቲያን ቢሆን መልካም ነው ። ምንም ይሁን ምን በርእሰ ብሔርነቱ ያለው ክብር ግን የአገር ክብር ነው ። ከቅዱስነታቸውም የምንማረው ይህንን ነው ።

## እንዴት ከመንበራቸው በግፍ እንዲሰደዱ ተደረጉ?

በዚህ ክፍል ላይ የአዲስ አበባው የሐሰት ጽሑፍ የሚጀምረው *"በመሠረቱ የቀድሞው አራተኛው ፓትርያርክ የነበሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስቆስ ሆነው ለመመረጥ በእጩነት ከቀረቡት ቆሞሳት መካከል በትምህርትም ሆነ በአገልግሎት ብቁ ሆነው በመገኘታቸው በኤጲስቆጶስነት መመረጣቸው አይዘነጋም"* በማለት ነው ። በዚህም ገና ለኤጲስ ቆጶስነት ሲመረጡ በሙያና በሥራ ብቁ መሆናቸውን አልካዱም ። መንፈስ ቅዱስ ፊታቸውን ጸፍቶ አፋቸውን ከፍቶ እውነት ስላናገራቸው የእውነት ባለቤት ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ። ሆኖም ግን አሁን የተናገሩት ተገድደው ስለ ሆነ ቅዱስ መጽሐፍ "ውሻ ወደ ትፋቱ ተመለሰ" እንደሚል ፣ ወደ ሐሰታቸው ይመለሳሉ ። ቅዱስ ፓትርያርኩን ያሳደዱበትና መንበሩን በሥርቆት የያዙበትን ምክንያት ሲናገሩ እንደ ተራ ሌባ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ምክንያቶችን ያቀርባሉ ።

1. *ከፓትርያክነት የወረዱት ራሳቸው በገዛ ፈቃዳቸው አውርዱኝ ብለው ነው ።*
2. *ከፓትርያርክነት የወረዱት የጤና እክል ስለ ገጠማቸው ነው ።*
3. *ከፓትርያርክነት ያወረዳቸው ሕዝበ ክርስቲያኑ ነው።*

*መጀመሪያ ዓይን ካወጣው ሐሰታቸው እንጀምር ።*

## 1/ እውን ቅዱስ ፓትርያርኩ በገዛ ፈቃዳቸው አውርዱኝ ብለዋል?

ሐሰተኛው የአዲስ አበባ ጽሑፍ ፓትርያርኩ ስለ ታመሙና መሥራት ስላልቻሉ በራሳቸው ፈቃድ ሥልጣን ለቀቁ ይላል ። ከሁሉ የሚገርመው የሁለት ሺ ዓመት ታሪክ ባለቤት የሆነች ፥ ከአርባ ሚሊየን በላይ አማኞች ያላት ቤተ ክርስቲያን መሪ በፈቃዳቸው የወረዱበትን ማስረጃ እነዚህ ወገኖች አለማቅረባቸው ነው ። ለምሳሌ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ልቅቄአለሁ ብለው ለሲኖዶሱ ሰጥተዋል ከተባለ በመጀመሪያ ይህን ጉዳይ ሲናገሩ ሲኖዶሱ ምልዓተ ጉባኤ አድርጎ መሆን አለበት ። ያ ሲሆን ደግሞ ይህ ጉዳይ በወቅቱ በቃለ ጉባኤ መያዝ ይኖርበታል ። የአድማና የተንኮል ቅንብር መሆኑ የሚታወቀው ቅዱስ ፓትርያርኩ በተገኙበት የተደረገ ስብሰባ አለመኖሩ ነው ። ተገኘ የተባለው መረጃ *«ሲኖዶሱ ስለአመማቸው ዕረፍት ያስፈልጋቸዋል አለ»* የሚል ነው ። ሥልጣኑን የያዘው አዲስ ቡድን ቤተ ክርስቲያኗን ሊያሠራ ባለመቻሉና የሲኖዶሱን አባላት ወከባ ስላበዛባቸው ፥ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አላደርግም በማለቱ ፥ ሲኖዶሱ ውክልና ተቀበለ እንጂ አላወረደም ። በዕረፍትም ይቆዩ የተባለው መንግሥት ልብ ገዝቶ ቤተ ክርስቲያኗን መጋፋቱን እስከሚያቆም ድረስ ሁኔታዎቹን ለማረጋጋት ሲኖዶሱ ወሰደው የተባለ እርምጃ እንጂ የቅዱስ ፓትርያርኩ ውሳኔ እልነበረም ። መለስ ብለን

ስናየውም አሁን በወቅቱ የመንግሥት ባለሥልጣናት የነበሩት ሰዎች ከሚሰጡት ምስክርነት አንጻር ቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ያህል አደጋ ውስጥ ወድቃ እንደ ነበር ለማየት እንችላለን ። ይህም ሊታወቅ በወቅቱ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ መሩት የተባለው ምልዓተ ጉባኤ የመሰብሰቡ ዋና ዓላማ «*በወቅቱ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ችግር መርምሮ መፍትሔ መስጠት*» የሚል ነው ። ወቅታዊ ችግር የተባለው የወያኔ መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ላይ የደቀነው አደጋ ነበር ። በመሆኑም በማስረጃነት የቀረበው ሰነድ የእነርሱን ሐሰት የሚደግፍ ሳይሆን እውነቱን የሚገልጥ ነው ።

ስለዚህ *ቅዱስ ፓትርያርኩ በፈቃዳቸው ነው የለቀቁት የሚለው*፣ አሉባልታ እንጂ እውነት አይደለም ። የቃልም ሆነ የጽሑፍ መረጃ የለውም ። የአዲስ አበባው ኃይል ዝናሩን ያራገፈበት የሐሰት መጽሐፍም ተጨባጭ መረጃ ማቅረብ አልቻለም ። ቅዱስነታቸውም በግዳጅ መሰደዳቸውን በየጊዜው እየተናገሩ ይገኛሉ ። መጀመሪያ ወደ ኬንያ እንደ ተሰደዱ ፥ ሁለተኛ አሜሪካ እንደ ገቡ ፥ በቅርቡም በ2005 ዓ.ም የጥምቀትን በዓል ምክንያት በማድረግ በሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ በቃልና በጽሑፍ ባስተላለፉት መልእክት ፥ በግፍ መሰደዳቸውን ተናግረዋል ። ነገር ግን እስከ ዛሬ ሰሚ አልተገኘም ።

## <u>የአዲስ አበባው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ የፈጸመው ታሪክ ይቅር የማይለው ስሕተት</u>

የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ፥ በሐዋርያት ቀኖና መሠረት ፥ ከሁለት በላይ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባኤ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የሚወክል ሲኖዶሳዊ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል ስለሚል ፥ ቀኖናዊነቱን በመርሕ ደረጃ እንቀበለው እንበል ። ግን በፓትርያርኩ ላይ የወሰደው ሲኖዶሳዊ ውሳኔ መጀመሪያ ቅዱስ ፓትርይሪኩን ለማውረድ ያደረገው ቀኖናዊ ግድፈት ፣ የሥነ ምግባር ችግር ሆኖባቸው አይደለም የወሰነው ። ምክንያቱም መንግሥት ፓትርያርያርኩ ካልወረዱ በጀት አልለቅም በማለቱ ምክንያት አባቱን ለመንግሥት ፈቃድ አሳልፎ በመስጠት ነው የወሰነው ። የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሕግ ጥሶ እውነተኛውን አባቱን አሳልፎ ሰጥቷል ። በመሆኑም ውሳኔው ቀኖናዊ አይደልም ። የአዲስ አባባው ሲኖዶስ የሠራቸው ስሕተቶችና ውሳኔውን የሲኖዶስ ውሳኔ  የማያሰኙት ዋና ዋና በደሎች የሚከተሉት ናቸው ።

**1/ <u>እውነትን ከዷል</u>** ይኸውም በሽግግሩ መንግሥት የታገደውን የሠራተኛውን ደመወዝና የቤተ ክህነቱን የሥራ ማስኬጃ በጀት ለማስለቀቅ ሲባል ቅዱስ ፓትርያርኩ ሳይታመሙ ታመዋል ብሎ የመንግሥትን ጉዳይ ለማስፈጸም ፥ አባቱን ስለ ካደ ነው ።

እንዲሁም ምንም ዓይነት የቀኖና ድጋፍ ሳይኖረው መንግሥትን ጋሻ በማድረግ  ቅዱስ ፓትርያሪኩን  ወርደዋል ማለቱ ነው ። የቤተ ክርስቲያኒቱን አባት መካድ ታላቅ በደል ሆኖ እያለ ይህም አልበቃ ብሎ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪ አባት ከመኖሪያ ቤታቸው እንዲወጡ ማስገደዱ ቀኖናዊ ነው ሊባል አይችልም ። ምን አልባት ሲኖዶሱ በደል መፈጸም እንጂ ኃላፊነትን መውሰድ ስለማይደፍር ሲኖዶስ ሳይሆን አባ ዜና ማርቆስ ናቸው ለማለት ይከጅል ይሆናል ። ከዚህስ ጋር ቅዱስ ፓትርያርኩን እንደ አባት ካለማስከበሩም በላይ ፥ እንደ አንድ ዜጋ እንኳ ሰብአዊ መብታቸውን ማስከበር አለመቻሉ ትልቅ ውርደትና የሚያሳፍርም ሆኖ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ይኖራል ።

አባቱን ያሰደደ ፥ ከዘመንተኛ መንግሥት ጋር በመተባበር ሀገረ ስብከት የሌለውን የቅዱስ ሲኖዶስ አባል እንኳ ያልነበረን ሰው ፓትርያርክ ብሎ የመደበ ሲኖዶስ በየትኛው የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ነው ሕጋዊ ሊሆን የሚችለው ። ሕጋዊነቱ በጠበንጃ ለሚጠብቀው የወያኔ ኢኃዲግ መንግሥት አምባ ገነናዊ ሥርዓት ብቻ ነው ።

**2/ <u>ሐሰት ተናግሯል</u>** ቅዱስነታቸው አለመታመማቸው እየታወቀ ፣ በሐሰት ሰብአዊ መብታቸውን ገፍፎ ታመዋል ብሎ መዋሸቱ ታላቅ በደል ነው ። *"በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር"* በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ሕግና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሚዛን ሲመዘን ፣ የሐሰት ምስክር ስለ ሆነ ፣ የሚሰጠው ብይን ሁሉ ተቀባይነት የለውም ። ስለዚህ ቀናናዊ ነኝ የሚለው የዲስ አበባው አካል ቀኖና እንዲህ ዓይነቱን አካሄድ ስለማይደግፍ ኢቀኖናዊ ነው ። የቅዱስ ፓትርያርኩ ጉዳይ የተወሰነው እርሳቸው በሰውነታችው ተጠይቀው የሆኑትን ተናግረው ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን ከመግሥት ቁጣ ለመታደግ በሚል ሰበብ ቅዱስነታቸው ያልሆኑትን ሆኑ ተብሎና የሲኖዶሱ ፍርሃት ችግር በቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ እንዲለጠፍ ተደርጎ ነው ። ቅዱስ ዳዊት  «ወሐሰት ርእሰ አመፃ» ያለውም እንዲህ ዓይነቱን ነበር ።

ቅዱስ ፓትርይርኩ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለቅቀዋል እያለ እስከ ዛሬ ድረስ ንስሐ በመግባት ፈንታ በሐሰት ላይ ሐሰት በመጨመር ሕገ እግዚአብሔርን በማፍረስ ላይ ነው ።

ስለዚህ ይህ ሲኖዶስ የሐሰት ምስክር በመሆኑ በፓትርያርኩ ላይ ወሰንኩት ያለው ሁሉ እንደ ቅዱስ ሲኖዶስ ተቈጥሮ

በውሳኔነት ሊጸድቅ አይችልም ። የጉዳዩን እውነተኝነት ለማጠናከር መጀመሪያ በሕገ ወጥነት ተመድበው የነበሩትን አባ ጳውሎስን ከምደባቸው ጀምሮ በሥልጣን ዘመናቸው የተሠራውንና አሁንም በወያኔ ተመርጠው የተሰጣቸውን ያጸደቁትን የሹመት ድራማና እየተከናወነ ያለውን እንቅስቃሴ መመልከት ይቻላል ።

ሌላው ቀርቶ ፓትርያርኩ ሳይታመሙ ተመዋል የሚለውን ስሕተት እንደ ስሕተት ብንመለከት የአዲስ አበባው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ ይህን ያለበትን የጊዜ ገደብ መመልከት ይጠቅማል ። የዚህን ሐሳብ ስህተት የሚያረጋግጠው ፓትርያርኩ ታመው መሥራት አልቻልም ብለው ቦታቸውን የለቀቁት መቼና የት ነው ? የሚለው ጥያቄ ሲመለስ ብቻ ነው ። ፓትርያርኩ ታመው ሥልጣናቸውን ለቀቁ የተባለው ወያኔ ኢሕአደግ መንግሥት ሆኖ አገር በተቆጣጠረበት ጊዜ ነው ። ዘመኑ ይኸውና ከሀያ ዓመት በላይ ሆነ ። ያን ጊዜ የታመመ ሰው እስከ አሁን ድረስ ያውም በስደት እንዴት ጤናማ ሆኖ ኖረ ? ነው ጥያቄው ። ይህንም የነሱን *"ሥልጣን የለቀቁት በጤና ምክንያት ነው"* የሚለውን ሐሳብ እንቀበል ብንል እንኳ ፣ ከሃያ ዓመት በኋላ ምክንያት አድርጎ ማቅረቡ ከጤናማ አእምሮ የመነጨ ጤናማ ሐሳብ አይደለም ። በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ብንመዝነውም ሚዛን ሊደፋ አይችልም ። የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፣ ሕጋዊ የፓትርያርክነት ሥልጣን በአዲስ አበባ በሚገኘው ሲኖዶስም ሊካድ የማይችል ሆኖ መቅረቡ እውነት ነው ።

## 3/ <u>በሕገ ወጥ መንገድ ፓትርያርክ ሹሟል</u>

የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሌላም ቀኖናዊ ስሕተት አለበት ፣ ይኸውም በቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ የተሳሳተው ሳይበቃ ፣ በሕይወት ባሉት ሕጋዊ ፓትርያርክ ላይ ምንም ዓይነት ውሳኔ ሳይሰጥ ፥ በሕገ ወጥ መንገድ አምስተኛ ፓትርያርክ መምረጡ ፥ በሕገ ቤተ ክርቲያን ላይ በደል ሠርቷል ። የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ለዚህ ክስ ቀኖናዊ መልስ የለውም ።

በድርድሩ ወቅት ፣ በሕመም ምክንያት መሥራት ስላልቻሉ ፣ በምትካቸው አባት ለመተካት የተወሰነው በምልዓተ ጉባኤ ስለ ሆነ ቀኖና ይፈቅዳል በሚል ያቀረበው መሚገቻም ከላይ በዘረዘርነው ምክንያት ውድቅ ሁኗል ።

ከዚህ በተጨማሪ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ እንደ ሲኖዶስ የማይቈጠርበት ዐቢይ ምክንያት አለ ። ይኸውም ፥ ያለ ምልዓተ ጉባኤ በተወሰኑ የወያኔ ኢሕአዴግ ደጋፊ ጳጳስት አስተባባሪነት ሕጋዊውን ሲኖዶስ ስላፈረሰ ፣ ዐቃቤ መንበር ብሎ የሾማቸው ሰውም የተመረጡት በምልዓተ ጉባኤ ስላልሆነ ነው ።

ስለ ሆነም በሕገ ወጡ ሲኖዶስ በተመረጡት ዐቃቤ መንበር አማካይነት ምልዓተ ጉባኤው ተጠራ ። ይህ ማለት ያለ ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ፥ በሕገ ወጥ መንገድ በመንግሥት ፈቃድ በተቀመጡት ዐቃቤ መንበር የተመራው ይህ ጉባኤ እንደ እውነተኛ ጉባኤ ተቈጥሮ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክል ቀኖናዊ መብት አልነበረውም ማለት ነው ።

በዚህም ምክንያት በስውር ተደራጅቶ የነበረው ቡድን የሲኖዶሱን አባላት በሥርዓት መጥራት አቅቶት ከሲኖዶስ ውጭ በመንግሥት አስተባባሪነት በተመደቡ ሽማግሌዎች አማላጅነት ነበር ጥሪውን ያደረገው ። በዚህ ሁሉ ምክንያት ሲኖዶሱ ቀኖናን የጣሰ ሕገ ወጥ ስለ ሆነ ፥ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክል ሲኖዶስ አይደለም እንላለን ።

## 2/ <u>ቅዱስ ፓትርያርኩ ኃላፊነታቸውን የማይወጡበት የጤና እክል አጋጥሞአቸዋልን ?</u>

በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀቁ በሚለው ሐሰት ላይ እንደ ጌጥ አልፎ አልፎ ጣል የሚያደረግበት ሌላው ምክንያት በጤና እክል ምክንያት ነው የሚል ነው ። ቅዱስ ፓትርያርኩ ከመንበራቸው ከተሰደዱ ከሃያ ሁለት ዓመታት በኋላ እንኳ እግዚአብሔር ኃይል ሆኖአቸው ፥ ቀድሰው የሚያቆርቡ ፥ ጳጳሳትን ፥ ካህናትን ፥ ዲያቆናትን የሚሾሙ ፥ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ በመሄድ ልጆቻቸውን የሚባርኩ በመሆናቸው ፥ ሥራቸው ፥ ተግባራቸው ፥ የሚታተኞችን አፍ የሚያዘጋ ስለ ሆነ ምንም አንልም ። መንበራቸውን ያስነጠቀውም የነጠቀውም ወደ እውነቱ ቦታ ስለ ሄዱ ፥ ፍርዱን የታሪክ ባለቤት ለሆነው ለልዑል እግዚአብሔር እንተወዋለን ።

ከተጻፈው የሐሰት ሰነድ ውስጥ ሰውን ያሰናክልልናል ብለው በዋናነት ያቀረቡት ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ይመሩት በነበረው የቋሚ ሲኖዶስ የተላለፈው ውሳኔ ነው ።

ጽሑፉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ እንዴት በግፍ ከመንበራቸው እንደ ተሰደዱ የሚያመለክት ነው ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ *"በሕመም ምክንያት መቀጠል ስለማልችል ሥልጣኔን ተረከቡኝ ብለዋል"* የተባለው በቃላቸው መሆኑን አውስቶ አንድም የጽሑፍ ማስረጃ አለማቅረቡ ፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በይፋ አለመናገራቸው አንደኛው ምክንያት ነው ። እንኳን ፓትርያርክ ተራ የቢሮ ተላላኪ እንኳ ሥራዬን እለቃለሁ ቢል "ጽፈሕ በማመልከቻ አስገባ" መባሉ አሁንም ያኔም የተለመደ አሠራር መሆኑ እየታወቀ ፥ ያለመረጃ ሲኖዶሱ በመንበረ ፓትርክናው ላይ ውሳኔ ይሰጣል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው ። (የቅዱስ ፓትርይርኩን ደብዳቤ ከዚህ በታች ይመልከቱ)

ጥር 25 ቀን 1994 ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ፤</u>

በፓትርያርክነት ሥልጣኔ ለ፰ ዓመት ከመራሁ በኋላ በ1984 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ለተወሰነ ጊዜ የነበረውን ወቅታዊ ሁኔታ ባገናዘበ ገለፃ ብቻ ለቅዱስ የታወቀ ነው፡

1ኛ/ ነሐሴ 20 ቀን 1983 ዓ.ም የተጻፈው የቅዱስ ሲኖዶስ ውሣኔ

2ኛ/ መስከረም 28 ቀን 1984 ዓ.ም የተጻፈው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ፓትርያርኩትን እንደሚቀ ተወሰኖ በቁጥር 69/298/84 የተጻፈውን አስታውሰሁ፡፡ በወቅቱ የነበረው የመንግስት ጊዜ አስቤያለሁ፤ ወሰው የኢትዮጵያ መንግስት ሁኔታ ሁኔታውን በአርጋታ እንከታተለው ቆትና እስኪ ያለኝት ቅዱስ ሲኖዶስም ከታሪክና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንፃር ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን ተወካይ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤ እስኪያስገኝ ድረስ ለጊዜው ለመስራት ብቻ ለቅዱስ አቀራረብ የሰላም ወሳኔ ነበር፡፡

ቅዱስ ሲኖዶስም ጉዳዩን የተመለከተው በዚሁ አንፃር እንደሆነ የመሰነው ይዘት ያመለክታል፡፡

ስለዚህ ያን ጊዜም ሆነ አሁን ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋርም ሆነ በግል ያሳብኝን መንፈሳዊ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችለኝ መንፈሳዊውያን ተግባራትን ከማከናወን የሚያግድ የጤና ሆነ የሌላ ችግር ያለብኝ መሆኑን ስገልጽ ቅዱስ ሲኖዶስም አባላት በሙሉ የሚያውቁት ነው፡፡ ከዚህም ጋር ሳስገነዝብ የምወደው ቤተ ክርስቲያናችን ካሁን በፊት በአሳስፈችው የረጅም ጊዜ ታሪክ እንደምንረዳው በየወቅቱ ያጋጠማት ችግር በታላቅ ሂደት ብዙ እንደሆነ የታወቀ ነው፤ በከባቸውም ለበጎ የተተረጸ ነው፡፡ መደፊትም ምን ዓይነት የታሪክ ዘዛት በህገር ወስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ ሊያስከትል የሚችል እንደሚኖር ወደፊት ሰጠኝ ያለው አይሰፍረውም፡፡ ይህን በተመለከተን ዘንድ በእኔም በኩንተኛ ሐዋርያ የሚችለውን ለመስጠል ከቀኖና ቤተክርስቲያን ጋር ለማገናኘት ቀኖና እውነተኛ ... ለቅዱስ ሲኖዶስ የሚገባ መሆኑን ከፍ ችንም ወገንዘብ ያረጋገጥናል፡፡

አባ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

....// 2

// 2 //

በላዩ እንደገለጽኩት ሁሉ ያለብኝን ወንጌላዊ ኃላፊነት ለመወጣት ወንጌላዊ ተግባሬንም በማከናወን የሚያጋጥመ የጤናም ሆነ የሌላ ችግር የሌለብኝ መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ ተረድቶ ትቅዱስ ሲኖዶስ ... ጉባኤ ... አባቶ በአበቸሁ ይገለጽልኛል በማለት አመለክታለሁ፡፡ወደፊትም እግዚአብሔር ወገኔን እንዲያስተባብረኝ በመፀለይ በቀ ይሆን ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ==============================//

"እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ"

አባ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ግልባጭ፡-

ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዚዳንት

ለክቡር አቶ ታምራት ላይኔ
የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር

ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ ሥራ አስኪያጅ

አዲስ አበባ

ሲኖዶሱ በሕክምና ሰበብ ቅዱስ ፓትርያርኩን ገለል ያደረገበት ምክንያት ፥ የዛሬው ቤተኛ አባይ ፀሐዬና ታምራት ላይኔ ቀን በቀን ቤተ ክርስቲያን ላይ ዛቻቸውን ማባባሳቸው ፥ የቤተ ክርስቲያን ሰላም በውጭ በጠመንጃ ኃይል በውስጥ ደግሞ ወያኔ በሰገሰጋቸው ካህናት ተብዬ ሰላዮች ብጥብጥ መፈጠሩ ነው ። ይህም ሊታወቅ አሁን በሕይወት ኑረው መልስ መስጠት የማይችሉት የፓትርያርኩ እንደራሴ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ጳፉት የተባለው ደብዳቤ እንዲህ ይነበባል ።

*«ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ፦ ነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓ.ም በተደረገው ቅዱስ ሲኖዶስ ቅዱስነትዎ በዕረፍትና በሕክምና እንዲቆዩ ሲደረግ ስለማረፊያ ቦታ ጉዳይም ቅዱስነተዎ በሚፈቅዱት እንዲሆን መወሰኑ ይታወሳል ። <u>ይሁን እንጂ ቅዱስነተዎ መንበረ ፓትርያርኩን ያልለቀቁ በመሆኑ ቀደም ሲል ከየአቅጣጫው የነበረው ግፊት አሁንም እንደ ቀጠለ ነው ። ስለዚህ ለቅዱስነትዎም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ሰላም ሊገኝ የሚችለው የቅዱስነትዎ መኖሪያ ቦታ ሲለወጥና መንበረ ፓትያርኩን ሲለቁ ስለ ሆነ...»</u>* ይላል ።

ይህም ሁለት ነገሮችን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ።
<u>አንደኛ</u> ቅዱስ ፓትርያርኩንም ቤተ ክርስቲያኒቱንም መንግሥት ዕረፍት መንሣቱን ፥<u>ሁለተኛ</u> ቅዱስነታቸውን በግፍና በግዳጅ መንበረ ፓትርያርኩን እንዲለቅቁ መደረጉን በግልጽ የሚያስረዳ ጽሑፍ ነው ።

በሌላ መልኩ ስናየው ደግሞ *"አምኛልና ሥልጣኔን ተረከቡኝ"* ያለ አባት ለምን በደብዳቤ እንዲለቅ ይገደዳል ፤ መንበረ ፓትርያርኩ የማን ሆነና ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሲታመሙ ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይምኖት በታመሙ ጊዜ መንበረ ፓትርያርክ እንዲለቁ አልተጠየቁም ነበር ። አባ ጳውሎስም በማይለቅ በሽታ ታመው ነበር ፣ ነገር ግን እስኪሞቱ እስራኤል አገር ድረስ ፥ ደቡብ አፍሪካ ድረስ እየላካችሁ አሳከማችኋቸው እንጂ ተመሳሳይ በደል አልፈጸማችሁባቸውም ። "ከንቱ ነገርን ለምን ትወድዳላችሁ ? ሐሰትንስ ለምን ትሻላችሁ" ? ፓትርያርኩ ታመዋል ያሰኘውም ፥ ከመንበረ ፓትርያርክ ያሳደዳቸውም ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ጠላት የሆነው ወያኔ ነው ።

በአዲስ አበባ ያለው ኃይል በወቅቱ የነበረውን ቅዱስ ፓትርያርኩን የማውረድ ደባ በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የተከናወነ አድርጎ ለማስቀመጥ ጥሮአል ። ይህንንም ያደረገው፥ ብፁነታቸው ዛሬ በአካለ ሥጋ ቁመው ከእነርሱ ጋር መፋረድ ስለማይችሉ ነው ። ነገር ግን በቅዱሳን ሰፈር ያሉት ብፁዕ አባታችን ሳይሆኑ የእውነት አምላክ እነዚህን ሰማዕተ ሐሰት ይፋረዳቸዋል ።

ለማንኛውም ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ቤተ ክርስቲያንን ከአጣብቂኝ ለማውጣት በጊዜያዊነት ቋሚ ሲኖዶሱ የወሰደው እርምጃ ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈል በር የከፈተ መሆኑን በመረዳት የመንግሥትን አካሄድ ቢቃወሙም ፥ እርሳቸውን በማስወገድ ፥ ወዲያው የኤርትራ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስትለይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በመካድ የኤርትራ ፓትርያርክ የሆኑት አባ ያዕቆብ ሥልጣኑን እንዲይዙ ተደረገ ። ይህም በጊዜው በሥልጣን ፍቅር ያበዱት የወያኔና የሻዕቢያ ዋና ዕቅድ ነበረ ።

## 3/ <u>ሕዝቡ ቅዱስ ፓትርያርኩ ይውረዱልን ብሎአልን ?</u>

የሕዝብ ጥያቄ የሚመለስበት አገር ቢሆን ሆኖ ባለፉት ዓመታት ፥ በገማ ዕንቁላል እየተመታ ፥ ጫማ እየተወረወረበት ፥ አባ ዲያብሎስ እየተባለ ፥ የቤተ ክርስቲያንን ክብር ያዋርድ የነበረው ከቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ዘወር ባለ ነበር ። የሕዝብ ተቃውሞ ከሥልጣን ቢያስወርድ ሆኖ የወያኔ መንግሥትም ለአንድ ቀን አያድርም ነበር ። ያለው በምን ኃይል እንደ ሆነ ሁላችንም እናውቃለን ። በብፁዕ ወቅዱስ ላይ ሰልፍ ያደረጉት ራሳቸውን የለወጡ የወያኔ ካድሬዎች ነበሩ ። አስተባባሪውም ራሱ ወያኔ ነበር ። ስለዚህ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ተቃዋሚ ፥ ሕዝብ ሳይሆን የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት ነው ። ተቃውሞውንም በሁለት ከፈለን ልናየው እንችላለን ።

1/ ከበረሃ ጀምሮ ያቀደውን ቤተ ክርስቲያኒቱን የማዳከምና አገሪቱንም በዘር የመከፋፈል ሥራው ቤተ ክርስቲያኒቱ እንቅፋት ስለ ሆነችበት እርሷን አፍርሶ ለእርሱ የምትገዛ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመፍጠር እንዲመቸው ነው ።

2/ ቅዱስ ፓትርያርኩ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንና አማራን አከርካሪውን ለመስበር የመጀመርያ እርምጃው ቅዱስ ፓትርያርኩን ማሳደድ ነው ።

ፖ.ሣ.ቁ. 1283
አ.አ.
ADD. ABABA

...ያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
...ዘር ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
...pian Orthodox Church Patriarchate
HEAD OFFICE

ቁጥር 2/5
No.
ሰኔ 18 ቀን 1983 ዓ/ም
Date ........ 19 ....

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ ።</u>

ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጉዳዩ የወቅቱ ሁኔታ ሰኔ 28 ቀን 1983 ዓ.ም ለኢ.ሕ.ዲ.ግ ጉዳዩ መንግሥት አቅርበን የነበረውን የክብሮ መግለጫ ደብዳቤ 6 ገጽ የሆነ በዚሁ ደብዳቤ አባሪነት አቅርበናል።

በዚሁ ደብዳቤ እንደተገለጸው ካለ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድና ፍላጎት ለደርግ መንግሥት ሥልጣን ማራዘሚያ ታስበው የተሾሙት ፓትርያርክ በምክንያትና ፍላጎት ከሥልጣን እንዲወርዱ ለማድረግ ጥረት ዶ/ር ማርቆስ ወሊቃውንት ገብር ቀደምና የጠቅ/ቤ.መሪ እንደመሆናቸው ወገን ትግሉን ለማከላከልና ፓትርያርኩን በሥልጣን ላይ ለማቆየት በተቀየሰው ታክቲክ ልዩ ልዩ የሰብሳቢ ጉዳ በማስፈረብ እንዲታሠሩና በመንከባከብ የፓትርያርኩ ደጋፊ የሆነ ሥራ አስኪያጅ እንዲመደብ ቀጥሮ የነበረው በቀጠናውና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የበላይ ባለሥልጣኖች ድጋፍ እንዲፈጸም ጥረት ተደርጓል ።

አሁንም የተሰጠ የፀብ ትግልና ውዥንብር በመንዛት የሥራ አስኪያጁ ቢሮ እንዲዘጋና ዓኛ ደጋፊዎች እንዲወጡ ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ስለሆነ የጠናው ጉዳዩን በወሬ ባኛና ለመንግሥት አቅርበን የነበረውን ደብዳቤ ፎቶ ኮፒ በመመልከት ትዕዛዝን እንዲሰጡልን ... ክብር እንዲያደርጉልንና መንግሥት ውዝግብ እንዲያስወግዱልን በኮሚቴው ስም አመለክታለሁ ።

“ኢትዮጵያ ትቅደም”

[signature]

መምሬ ፍሥሐ ጉበዚ
የሰንበት ትምህርት ቤቶች መምሪያ ኃላፊ

የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት ይህን ሥራ ለማከናወን ብዙ ዘዴዎችን ተጠቅሟል አንደኛው የተለመደውን የቋንቋ የዘር መሥመር በመከተል የራሱን ካድሬዎች የካህናት ልብስ በማልበስ ጭቁን የካህናት ማኅበር በሚል ዐመፅ መፍጠራቸው ነው። በዚህ አፍራሽ ቡድን አማካይነት የቤተ ክህነቱን ሥልጣን እጅ ለማድረግ ቅዱስነታቸውን ከመንበራቸው ለማውረድ የጀመሩት እንቅስቃሴ ሲሆን ፣

ሁለተኛው ፥ የመንግሥት ለውጥ በመጣ ቍጥር ፓትርያርክ በማስገደልና የለውጥ ዓርበኛ በመሆን የታወቁ ጥቂት የቤተ ክህነት ክፉ ሰዎችን በመግዛት በቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ የቤተ ክህነት ሰዎችን ለዐመፅ ማነሣሣት ነበር ።

ይህ ሆኖ እያለ *'ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ሕዝቡ ስለ ተቃወማቸው ፥ መንግሥት የሰጠውን የዴሞክራሲ መብት ተጠቅሞ ሕዝቡ ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ'* የሚለው ፍጹም ሐሰት ነው ። ተቃዋሚው የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት እንጂ ሕዝብ አይደለም ። ሰላማዊ ሰልፉንም ያደረገው የወያኔ መንግሥት ነው ። መቸም እርሱን የማይደግፍ ሰላማዊ ሰልፍ እንደማይፈቅድ ወያኔን የሚያውቀው ያውቀዋል ። እንኳን ያን ጊዜ ይቅርና አሁን እንኳ በነጻነት የመሰብሰብ ፥ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት ፥በሀገራችን የለም ። እንኳን መንግሥትን በመቃወም ዜጎች ሰልፍ ሊወጡ የግራዚያኒን ክብር ተቃውመው ሰልፍ የወጡትን ኢትዮጵያንን እንኳ የሚያስር የፋሺሽት ደጋፊ ጉደኛ መንግሥት ነው ወያኔ ።

ሕዝብማ ፓትርያርኩን ደግፎ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ከተማውን ያጥለቀልቀ ሰልፍ አካሂዶ ነበር ። የአዲስ አባባ አድባራትና ገደማት አስተዳዳሪዎች የሰበካ ጉባኤ አባላት ፥ የምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት የካህናት ተወካዮች በቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ ሕገ ወጦች የሚያካሂዱትን የስም ማጥፋት ዘመቻ አንያዲያቆሙና የሽግግር መንግሥትም እጁን ከቤተ ክርቲያን ላይ እንዲያሣ በነሐሴ 18 ተሰብስበው የወሰኑትን ወሳኔ በመገናኛ ዘዴዎች እንዳይነገር ከፍተኛ አፈና ተደርጎአል ። ሆኖም እውነቱ ከቤተ ክርስቲያን ልጆች የተሰወረ አይደለም ። የቅዱስ ፓትርያርኩን ስም ለማጥፋት ወደ ደብረ ሊባኖስ የሄዱትን የወያኔን አሽከሮች ፥ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አባቶች አሳፍረውና ቅዱስ ፓትርያርኩን ደግፈው የመለሷቸውን ማንም አይረሳውም ።

የጎንደር ሀገር ስብከት ምእመናንና ካህናት ያቀርቡትን የቅዱስ ፓትርየርኩን ድጋፍ የመንግሥትን ተቃውሞ እንዴት ሸሸጋቸሁት ? የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሠራተኛ ቤተ ክርስቲያኒቱን የከዳውን የጠቅላይ ቤተ ክህነቱን ሥራ አስኪያጅ ማባረሩንና በኋላ ይኸው ሰው ለወያኔ ባቀረበው ድጋፍ መንግሥት ሊያስጠብቅለት ወስኖ ሳለ ግለሰቡ በነበረው የሙስና ሥራ ወደ እሥር ቤት መውረዱ ይታወሳል ። አዲስ አበባ ያሉት አባቶች ። የረሱት ወይም ሊያምኑት የማይፈልጉት ይህንን ሁሉ እውነት ነው ። (የጎንደር ሀገር ስብከት ምእመናንና ካህናት ቅዱስ ፓትርይርኩን በመደገፍ የላኩትን ደብዳቤ ከዚህ ቀጠሎ ይመልከቱ)

ቀን 25/10/84 ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ጠቅላይ ፓትርያርክ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ።

5ኛውን ፓትርያርክ ምርጫ በተመለከተ በክልሎችን ወረዳ ተወካዮችን ወርወን እንድንልክ በተላለፈልን ቁ.ቁ. ደብዳቤ መሰረት በሃገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሰብሳቢነት በወገራ ወንገ ሰት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ወንጌል አዳራሽ ተገኝተን ጉዳዩ በሰፊው ተገለጸ ልን ከተወያየንበት በኋላ በዚህ የፓትርያርክ ምርጫ ጉዳይ በ1983 ዓ.ም ተመሳሳይ ትእዛዝ ተላልፎልን የቤተክህነቱ የፍትሐ ነገሥት ሕግና ስርዓት የሚያፋልሰውን ሆኖ በመገኘቱ ፓትርያርኩ በህይወት እያሉ በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ አይመረጥም በማለት ተቃውመን ጉዳዩ እስከ ዘርፍ ጠቅላይ ሚኒስትሬ ድረስ መድረሱን እናስታውሳለን።

አሁን ደግሞ ይህ ጉዳይ ሳይፈታ በሌላ ወሰኑ የምርጫው ተግባር እንደገና መጋበዛችን የሐይማኖታችን ስርዓት በማይፈቅደው መንገድ የቀረበ በመሆኑ በዓለም ህዝብ ዘንድም መዘባበቻ የሚያደርገን ስለሆነ የምርጫው ተግባር አንሆንም በማለት 156 የአድባራትና የገዳማት አለቆች የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች፣ የሰበካ ጉባኤ ተወካዮች፣ የምዕመናን ተወካዮች በ22/10/84ዓ.ም ያሳለፍነው ውሳኔ በማግስቱ በ23/10/84 በዜና ማሰራጫ መነገሩ ይታወሳል።

በዚህ ስብሰባ የቤተ ክህነቱ ዋና ጸሐፊ ሊቀ ኅሩያን ገ/መስቀል ዘሩ አበምኔት ሰብሳቢነት ተገኝተው በውሳኔአችን ተካፋይ ሆነዋል። በድምጽ የተለዩ ሁለት ሰዎችም ከእርሱ ××××× ውጭ ናቸው።

ነገር ግን ግለሰቡ በቤተ ክርስቲያን አመራር ስልጣን ላይ ተቀምጠ በማናለብኝነት የጠቅላይ አድባራትና ገዳማት አገልጋዮ የምዕመናንና የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችን ድምጽ በመርገጥ ተወካዮች ተሰባስበን ውሳኔ አንሳለፍ ነን በዜና ማሰራጫ ያስተላለፍነውን የሃሰት ቃል በማድረግ ያስመረጥናቸውን ግለሰቦች እንደመረጥናቸው አድርጎ በ24/10/84 በዜና ማሠራጫ የማስተባበያ ቃል ማስተላለፉን አቋቁመናል።

ይህ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር አለመግባባትን ፍራቻን የሚፈጥር በመሆኑ ድርጊቱን በከፍተኛ ደረጃ እናወግዘዋለን።

በለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን አስጸያፊ ተግባር በቅዱሱ ሲተመለከተው በለማድገባ ግለሰቡ በፈጸመው ድርጊት ለፍርድ ወቅረቡ ባይቻለ እንደ በቃልው በማይመለከተው ስልጣን ውስጥ ገብቶ ያስተላለፈው የሃሰት ቃል ተቀባይነት እንዳያገኝ እንዲደረግለን በገሎ ወርደ የሳካ ትው ግለሰቡ ጉዳዩን የሚይወክሉ መሆናቸው እንዲታወቅልን።

በሌላው በኩል በ22/10/84 ዓ.ም ባሳለፍነው ውሳኔ በዜና ማሰራጫ በተነገረው ውሳኔአችን የጸናን በዚህ በተካሄደ ምርጫ የማንካፈል መሆናችንን እንዲታወቅልን በትህትና እናሳስባለን።

የጎንደር አድባራትና ገዳማት አለቆች፣
ተወካዮች፣ የምዕመናንና የሰንበት ት/ቤት
ተማሪዎች በሙሉ

[illegible]

ግልባጭ
ለጎንደር ዜና አገልግሎት ለ/ቤት
[illegible]



# ቅዱስ ፓትርያርኩ ለምን ተሰደዱ ?

ሕዝቡን በዘር ሲከፋፍል ፥ በገዛ ሀገሩ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲኖር ሲያደርግ የኖረው ክፍል ፣ ቅዱስ ፓትርያርኩንም ያለ ምክንያት ተሰደዱ እያለ ያላዝናል ። በአረጋዊነታቸው ፥ ከቅድስት አገር ተነጥለው እንዲሰደዱ ያደረጋቸው ይኸው አካል *«ያለ ምንም ምክንያት ነው»* ይላል ። ምንም እንኳ እውነቱን ደብቀው ሐሰትን ፀንሰው የሚጽፉ የአመፃ ልጆች መሆናቸውን ብናውቅም ፥ ለቤተ ክርስቲያናችን ልጆች ሳንደክም ሳንሰለች እውነቱን አሁንም ደግመን ደጋግመን እንናገራለን ።

## 1/ ቅዱስ ፓትርያርኩ የተሰደዱት ሥራቸውን ማከናወን በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ስለ ሆኑ ነው ።

ኢሕአዴግ በበርሃ እየፈከረ እንደ መጣ መጀመርያ የከፋት ዓላማው ያደረጋቸው የኢትዮጵያውያን የአንድነት ምልክት የሆኑትን ተቋማት ነበር ። ተቀዳሚዋ ተጠቂም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት ። ለዚህም ነበር በቅድሚያ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪ አልቀበልም ፥ በስማቸው የሚተላለፈውን ሕጋዊ ሰነድ ሁሉ አልቀበለም ያለው ። በፓትርያርኩ ስም ቤተ ክርስቲያኒቱ ምንም አይነት ሕጋዊ ግንኙነት ከማንኛው አካል ጋር ልታደርግ አትችልም ብሎ የቤተ ክርስቲያኒቱንም በጀት እንዳይንቀሳቀስ አግዶ ፥ ሠራተኞቿም የወር ደመወዛቸውን እንዳያገኙ በማገድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ግፍ ይፈጽም ነበር ። በዚህ ቀውጢ ጊዜ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሠራተኞችም ፥ ቅዱስ ሲኖዶስም በአንድነት ቆሞ አባታችንን አናስነካም በማለት በጽንዓት መቆማቸው ይታወሳል ።

## 2/ ቅዱስ ፓትርያርኩ የተሰደዱት ወያኔ በገሀድ ከመንበራቸው ስላሳደዳቸው ነው ።

ከላይ እንደ ጠቀስነው ቤተ ክርስቲያንን ከወቅታዊው የመንግሥት ጫና እንታደግ የሚል ፍርሃት የወለደውን ጥያቄ ሲኖዶሱ ፀነሰ ። የለም ፓትርያርኩ ታመሙ እንበልና እኛ ሥራውን እንሥራ በኋላ ሁሉም ሲረጋጋ ቅዱስነታቸው በሰላም ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ይቻላል የሚል ውሳኔ ላይ ደረሰ ። ስለዚህ ፓትርይርኩ ሳይታመሙ ታመዋል ተብለው ተነገራቸው ። በእርግጥ ደዌያቸው ወያኔ ኢሕአዴግ ነበር እንጂ የሥጋ ደዌ አልነበረም ። ይህ ሁሉ ሲሆን ቅዱስ ፓትርያርኩ በትዕግሥት ይመለከቱ ነበር ። ከዚያም በመንግሥት አስፈራሪነት መንበረ ፓትርያርኩን ለቀው በግዳጅ እንዲወጡ ተደረገ ። ስም የተሰጠው *«በሕክምናና በጸበል እየተረዱ»* የሚል ነበር ። እስከዚህ ድረስ ብዙዎቹ አባቶች አብረው እየተሰበሰቡ ስለ ነበር ከጥቂቶቹ በቀር ብዙዎቹ ፍርሃት የወለደው የዚህ ምክንያት ተጠቂዎች ነበሩ ። ከዚህ በኋላ ግን መንግሥት ሲኖዶሱን በተነ ጽ/ቤቱንም አሸገ ።

የወያኔ መንግሥት ይህ በቂ አይደለም ከሥልጣናቸው ወርደዋል የሚል መግለጫ ያስፈልጋል በአስቸኳይ ማውረድ አለባችሁ አለ ። ሲኖዶሱ ከተበተነ በኋላ የወያኔና በዚያ ጊዜ በፍቅር ላይ የነበሩት የሻዕቢያ መሣሪያዎች የሆኑትን አሰባስቦ ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ሰየመ ። ከዚህ በኋላ በሕገ ወጡ አቃቤ መንበር በአቡነ ያዕቆብ ሰብሳቢነት ፓትርያርኩ ወርደዋል የሚል መግለጫ ተሰጠ ። ቅዱስ ፓትርያርኩን የሚደግፉ ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፎች ቢደረጉም የዜና ሽፋን ተነፈጋቸው ። ሀገረ ስብከቶች ፥ገዳማትና አድባራት ቢቃወሙም ሰሚ ዳኛ ጠፍቶ በግፍ እንዲወርዱ ተደረገ ። ከሞት ወይም ከእስራት በቀር ያልተፈጸመባቸው ነገር አልነበረም ፣ ባይሰደዱ ሆኖ እሱም ቢሆን አይቀርላቸውም ነበር ። ቅዱስ ፓትርይርኩን አውርደናል ብለው ሲወስኑ የቅዱስ ሲኖዶስ የምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ አልነበረም ። ቋሚ ሲኖዶስም ተበትኖ ነበር ።

በዚህ ወቅት ነው እውነትን በመናገር የታወቁት ፥ እውነተኛው ምስክር ፥ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ፥ *«ቅዱስ ሲኖዶስ የወንበዴዎች ዋሻ ሆነ»* በማለት የጻፉት ። ይህንንም ያሉበት ምክንያት ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ማስከበር የተሳነው ሲኖዶስ ፥ ወንበዴዎችን የሚያስተናግድ ፥ አባቱን የሚያሳድድ በመሆኑ ነበር ።

መንግሥትም የነበረውን ሲኖዶስ በትኖ ዓላማውን ለማስፈጸምና እርሱ አስቀድሞ ያዘጋጀውን ሰው ለማስቀመጥ ላይ ታች ማለት ያዘ ። ቅዱስ ፓትርያርኩም ፍጹም ጤነኛ መሆናቸውን የተሰጣቸውን አደራ ለመወጣት እንደ ቀድሞው አሁንም ዝግጁ መሆናቸውን ጠቅሰው ጻፉ ፣ ግን ሰሚ አልተገኘም ።

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

<u>የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት</u>

ቁጥር 60-ጠ2/02/44 ቀን 27/12/83

ለገንዘብ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ፣</u>

የቤተክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት በጀት በችግሩ ሥራ ለመቢያጃ ትዕዛዝ እንዲደረግ የቀረበውን ጥያቄን ለማወቅ ተችሏል:: ለበጀቱ የበጀቱ የቤተክህነቱ አስተዳደር በሚመለከት ውስጥ ለመጠበቅ ይርስ አሁን በቤተ ክህነቱ በሰራተኞች ያለው ችግር ለማቃለል እንዲቻል የደመዝ በጀት ብቻ ተለይቶ የቤተክርስቲያኑ ሲኖዶስ በሚወስነው ሰው ፊርማ ወጪ እንዲሆን የተፈቀደ መሆኑን እስታውቃለሁ::

በሠላምታ ጋር

ታምራት ላይኔ

ጠቅላይ ሚኒስትር

ግልባጭ፣

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን

የሲኖዶስ ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ቁጥር 6/ዟ7/1561/85
Ref. No.

ጀ1/3/ቀን ፲፱፻85 ዓ.ም
Date

አባ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
*Abba Paulos*
*PATRIARCH OF ETHIOPIA*

ለኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
አዲስ አበባ፤

ጉዳዩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክን ይመለከታል።

ጉድዩ ከላይ በስም የተጠቀሱት ፓትርያርክ የኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ሳያውቀው የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ ቤት የሆነውን እንድ ማርቼዲስ መኪና በመያዝ ራሳቸውና አንድ ሹፌር ሌላውም ከእርሳቸው የነበረው ዲያቆን ልሣነወርቅ የሚባል ልጅ ጋር በመሆን ከኢትዮጵያ ሞያሌ በኩል አድርገው ሶስት ራሳቸው ሆነው መስከረም 30 ቀን 1985 ዓም ወደ ኬኒያ የኮበለሉ መሆናቸው ታወቋል።

እንደት ከሀገር ለቀው የወጡበት በምን አይነት ቅንብር እንደሆነ፣ ቅዱስ ሲኖዶሱ የማያውቀው በመሆኑ በኢትዮጵያ ፖሊስ ኮምሽንና በሀገር ውስጥ ደህንነት ኢሚግሬሽን ጉዳይ ጽ ቤት እንደት አድርገው እንደወጡ እንዲያጣራልን እየገለጽን፤ ከላይ የተጠቀሱት ፓትርያርክ አባ መርቆሬዎስ ኬኒያ የገቡ መሆናቸው በኢትዮጵያ ሬዲዮንና ቴሌቪዥን የተገለጸ ሲሆን በእናንተ በኩል ኬኒያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ክትትል እንዲያደርግልንና ጉዳዩን አጣርቶ አፈጻጸሙን የኢትዮጵያ መንግሥት ግንዛቤ ውስጥ እንዲያስገባል እየገለፅን ማለትም ከኬኒያ ወደ ሶስተኛ ሀገር እንዳይወጡ ለኬኒያ መንግሥትና በዓለም ዙርያ የሚገኙ ሀገሮችና ኤምባሲዎች ጥብቅ ደብዳቤ እንዲጻፍልን ቢቻል ፓትርያርኩ ከኬኒያ ተይዘው ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱበትን የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያዘጋጅልን በታላቅ አክብሮት እንገልጻለን።

" እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ "

አባ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት
Abba Paulos
Patriarch of Ehiopia
and Echegue of the See of St. Tekle Haimanot,

ግልባጭ ፣

ለብጭ ፦ ለክልል 14 መስተዳድር ጽ/ቤት
፦ ለክልል 14 ፖሊስ ኮሚሽን ጽ/ቤት
፦ ለመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
፦ ለአዲስ አባባ ሃገረ ስብከት ጽ/ቤት

አዲስ አባባ

አዲስ አበባ
ADDIS ABABA
FAX 55 22 11

ከዚህ ሁሉ በኋላ ቅዱስ ፓትርያርኩ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ቤት ተከራይተው አስቀመጧቸው ። ከየት ወደቁ ባይም አልነበረም ።

ይህ በዚህ እንዳለ ሐምሌ አምስት ቀን ቅዱስ ፓትርይርኩ አዲስ አበባ እያሉ በላያቸው ላይ ሌላ ለመንግሥት ታማኝ የሆነ ሰው በመግሥት ተሾመና ኢሕአዴግ በይፋ ቤተ ክርስቲያኒቱን ተቆጣጠረ ። በዚህ ጊዜ *«ወኢይደሉ ከመ ትኩን ዛቲ ሢመት ለክልኤቱ በአሐዱ ዘመን ፥ ወበአሐዱ መንበር ። ወእመሰ ኮነ ዝ በአሐዱ ሀገር ትጽናዕ ለዘተሠይመ ቅድመ ።*
*ይህች ሹመት በአንድ ዘመንና በአንድ መንበር ለሁለት ሰዎች ልትሆን አይገባም ። ይህ በአንድ አገር ከተደረገ ግን ፥ አስቀድሞ ለተሾመው ትጽና»* የሚለው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፈረሰ ። ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 4 ቍጥር 70 ።
ይህ ሁሉ ሲሆን ቅዱስ ፓትርያርኩ በትዕግሥት ሁሉን ይከታተሉ ነበር ።

ከዚህ በኋላ በከተማው ውስጥ መኖራቸው ስለሚታወቅ ፣ ቅዱስ ፓትርያርኩ በሕይወት ካሉ መንግሥት ለሾማቸው ለአባ ጳውሎስ ሕዝቡ አክብሮት አይኖረውምና አንድ ነገር መደረግ አለበት ተብሎ ተመከረ ። ምክሩም ወደ እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ሄደው ከአንድ መቃብር ቤት እንዲቀመጡ ነበር ። ይህም ማናቸውንም ነገር ለማድረግ ያመቻል ተባለ ። ቅዱስ ጳውሎስን ሳንገድል እህል አንቀምስም ብለው የተማማሉትን ሰዎች ምክር እንደ ሰማውና ወደ ሮም በስደት እንዲሄድ እንዳደረገው ወጣት ፥ ክፉ ምክራቸውን የሰማ አንድ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ደባቸውን ገለጠው ። ከዚህ በኋላ ወደ እግዚአብሔር በጾምና በጸሎት ሲያመለክቱ ቆይተው ፥ አባ ጳውሎስ ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓ.ም መንበሩን በኃይል ከያዙ ከሁለት ወር በኋላ ፥ ቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ ኬንያ ተሰደዱ ። በተሰደዱበት ሀገር በኬንያም ዕረፍት ላለመስጠት አሳዳጆቻቸው ሌትና ቀን ይደክሙ ነበር ።

በዚያም በከባድ እንግልትና መከራ አምስት ዓመታትን አሳልፈዋል ። እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ ከዘመኑ ባለሥልጣናት ጋር ወግነው አባታቸውን ያሳደዱ ሰዎች *"ማንም ሳይነካቸውና ምንም ሳይሆኑ መንጋውን በትነው ተሰደዱ"* እያሉ በሐሰት የሚጽፉ ሁነዋል ።

## <u>3. የቅዱስነታቸው ስደት የክብር ስደት ነው ።</u>

በመሠረቱ መሰደድ በራሱ ሰማዕትነት ነው ። ሰማዕትነት ብዙ ዓይነት ነው ። ከእነዚህም ለእውነት የሚሆን ፥ ያለ ደም የሚሆን ሰማዕትነት ነው። *«ሰማዕት ዘእንበለ ደም»* ይላሉ አባቶቻችን ። እመቤታችንንም *«እሞሙ ለሰማዕት»* ያሰኛት አንድያ ልጇን ይዛ ከአገር ወደ አገር መሰደዷ ነው ። ነቢያትም ጊዜ በሰጣቸው ሐሳውያን ሲሰደዱ ኖረዋል ። ጌታችንም *«ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ ያሳድዷቸው ነበርና»* ብሏል ። /ማቴ 5 ፥15/።

ሊቀ ካህናት ሰያሜ ካህናት ክርስቶስም ራሱ ተሰዶ ስደትን ባርኮታል ። የሱም አሳዳጆች ፥ ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ ይነሣል የሚለውን ተስፋ የሚፈሩ ፥ የዚያ ዘመን ፖለቲከኞች ሄሮድሳውያን ነበሩ ። እንዲሁ በትምህርቱ *"ከአንዱ አገር ቢያሳድዷችሁ ወደ ሌላዋ አገር ተሰደዱ"* ብሎ ለተከታዮቹ መመሪያ ሰጥቶአል ። አይሁድ በግፍ የሰቀሉት የክርስቶስ ነገር ሲነሣ እንደ እግር እሳት ያቃጥላቸው እንደ ነበር ፣ እንዲሁ የአዲስ አበባዎቹ አሳዳጆችም እግዚአብሔር በአባታችን ስደት እንደ ከበረ ሲሰሙ በመጸጸት ፈንታ ይረበሻሉ ። ስለዚህ ሰማዕተ ሐሰት ሆነው ከፍተኛ የጥላቻ ወሬን ያስወራሉ ። መገፋታቸው አንሶ ለምን አልሞቱም እያሉ ያስወራሉ ።

ሥልጣን ፈልገው ወንድማቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰዎች ፥ በግፍ ያሳደዷችውን አባት እስከ አሁን ድረስ ለምን አልሞተም በማለት በድፍረት ይናገራሉ ።

ቅዱስ ፓትርያርኩም ሆኑ ከእርሳቸው ጋር አብረው የተሰደዱት ወንድሞቻቸው ግን የስደተኞች አምላክ ስደታቸውን ባርኮላቸው እነሆ ፍሬያማ ሁነዋል ። ዓለም በኢኮኖሚ ቀውስ እየተጨነቀ ባለበት በአሁኑ ወቅት ፥ ምእመናን በሃይማኖት ጸንተው አብያተ ክርስቲያናትን እያነጹ ይገኛሉ ። ዛሬ በመላው ዓለም ያሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች « ተዋሕዶ ሃይማኖቴ ፥ መርቆሬዎስ አባቴ» ብለዋል ። ቅዱስ አባታችንም ምንም እንኳ ከልዑል እግዚአብሔር የተቀበሉትን የኢትዮጵያን ሕዝብ በቅርበት ሆነው ለማጽናና ባለመቻላቸው ቢያዝኑም ፥ በስደት ካለው ሕዝባቸው ጋር በመሆን በጾምና በጸሎት የአገራቸውን ችግር ወደ ልዑል እግዚአብሔር እያቀረቡ ይገኛሉ ። በቅዱስ አባታችን የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስም ፥ አንደበት ለሌለውና ነጻነቱን ለተነፈገው ሕዝባችን አንደበት በመሆን ስለ ሕዝባችን ክብርና ነጻነት ፥ ግፉን መከራውን ለዓለም ሕዝብ በማሳወቅ ላይ ነው ።

**አባ መርቆሬዎስ**
**ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ቀን ጥር 10 ቀን 2005 ዓ.ም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ከሁሉ አስቀድሞ በመላው ዓለም የምትኖሩ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ካህናትና ዲያቆናት፣ ክርስቶሳውያን ምእመናንና ምእመናት እንዲሁም ኢትዮጵያውያን የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ ሁላችሁ ምሕረቱና ቸርነቱ የማያልቅበት አምላካችን እግዚአብሔር በሕይወትና በሰላም ጠብቆ እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ።

*"ወናሁ መጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘቦቱ ሠመርኩ።"*
*"ለተዋሕዶ የመረጥኩት፣ በእርሱ ህልው ሆኜ ልመለክበት የወደድሁት ልጄ ይህ ነው።" (ማቴ 3፥17)*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ጥምቀት ስታከብር የእግዚአብሔርን ታላቅ የአድኅኖት ሥራ ታስባለች። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚመሰክሩት ክርስቶስ በሠላሳ ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቋል፤ በዚህም ማየት በጥምቀቱ ተቀድሰዋል፤ የሰዎች ሁሉ የዕዳ ደብዳቤ ተደምስሷል። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ጥል በጥምቀቱ ተሽሯል። ይኸውም ቅዱስ መጽሐፍ "ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ፤ እነሆ ሰማያት ተከፈቱ" ሲል እንደገለጸው በኖኅ ዘመን የጥፋት ውኃን ያዘነመው ሰማይ ዛሬ በክርስቶስ ጥምቀት ለአንድነትና ለሰላም ተከፍቷል። ዳግመኛም ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ለመወለድ የምታስችለንን ጥምቀት በቸርነቱ መሥርቶልናል። አብ ከሰማይ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ ሲመሰክር፣ ወልድ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ፣ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ በወልድ ላይ ሲያርፍ የእግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት ምሥጢር በጥምቀት ተገልጧል። በመሆኑም ጥምቀት ታላቅ ሃይማኖታዊ በዓል ነው። ጥምቀት የቤተ ክርስቲያን የነጻነት በዓል ነው። ጥምቀት የሰላምና የፍቅር የአንድነት በዓል ነው። ጥምቀት የክርስቶስ ፍቅርና ክብር በአደባባይ የተገለጠበት በዓል ነው። ስለዚህ ሐዋርያዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በፍጹም መንፈሳዊ ደስታ ታከብረዋለች።

**1152 S Stone Mountain Lithonia, GA 30058 Phone: (770) 469-5462 P.O. Box 711 Stone Mountain, GA 30086**

**አባ መርቆሬዎስ**
**ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ዛሬ ጥምቀትን በሎስ አንጀለስ ከተማ የምናከብረው በእግዚአብሔር ፈቃድና ውሳኔ ነው። በመሠረቱ ሁላችንም ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ስላጋጠመን ለመሰደድ በቅተናል፤ በምንወዳት ሀገራችን ላይ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል፣ ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበልነውን መለኮታዊ አደራም ለመወጣት እየሠራን ሳለ በውስጥ ቢጽ ሐሳውያን በውጭ ደግሞ የዚህ ዓለም ባለሥልጣናት ተቃውሞ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኖብን ነበር። ነገር ግን "ኢየሱስ ስዱድ ተሰፋሆሙ ለስዱዳን" የተባለው ክርስቶስ በባዕድ ምድርም ሐዋርያዊ ተልኳችንን እንድናከናውን ፈቅዶልናል። እነሆ ቸሩ አምላካችን የባዕዳንን ምድር ባርኮ ለአብርሃምና ለዘሩ እንደሰጠ የእኛንም ሕዝብ በተበተነበት ዓለም ሁሉ አብዝቶ እየባረከው ይገኛል። ይልቁንም በዓለም ሲገፉ የኖሩት ቅዱሳን አባቶቻችን በረከትና ረድኤት አንድም ቀን እንኳ አልተለየንም። እግዚአብሔርም ምድርና መላዋ የእርሱ ስለሆነች እርሱ ባኖረን እየኖርን ቤተ ክርስቲያናችንን በማገልገል ላይ እንገኛለን። ብዙ ሰዎች ለምን አይናገሩም? ስለራስዎ ተናገሩ ይሉኛል፤ ነገር ግን እኔ ለሚሰማኝ አምላኬ ዘወትር እየተናገርኩ ስለሆነ አንድም ቀን ዝም እንዳላልኩ ሁሉም ሊገነዘብ ይገባል።

ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ዝም አላልኩም። በቅርቡ በኢትዮጵያ ወዳሉት አባቶችም ሐሳብዎን በደብዳቤ ይግለጹልን ብለው በጠየቁኝ መሠረት ጽፌላቸው ነበር። ነገር ግን አልሰሙም። እኛ በኢትዮጵያ ያለችውን ቤተ ክርስቲያናችንን ዘወትር እናስባታለን፤ ወንድሞቻችንንና ሀገራችንን እንናፍቃቸዋለን። ምንም እንኳን ከሀገራችን ብንርቅም በመንፈስና በጸሎት በኢትዮጵያም ሆነ በመላው ከተበተነው ሕዝባችን አልራቅንም። ይልቁንም በዓለም የተበተነውን ሕዝባችንን ዘወትር በማጽናናትና ቤተ ክርስቲያንን በውጭው ዓለም እንድትስፋፋና እንድትጠናከር፣ ከሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር በፈቃደ እግዚአብሔር ስደተኛው ሕይወታችን በፈቀደልን መጠን በመሥራት ላይ ነን። የልባችን ምኞትና ናፍቆት ግን ቤተ ክርስቲያንን አንድ አድርጎ ማለፍ በመሆኑ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት የሚሠራ ኮሚቴ በቅዱስ ሲኖዶስ ተሰይሞ በብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ መሪነት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅም ሁላችንን ወክለው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠበቅና


1152 S Stone Mountain Lithonia, GA 30058 Phone: (770) 469-5462 P.O. Box 711 Stone Mountain, GA 30086

**አባ መርቆሬዎስ**
**ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ቤተ ክርስቲያንንም አንድ ለማድረግ ስለሚያደርጉት ከፍተኛ ጥረት ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ነገም ታመሰግናችዋለች።

እኛ ሳናልፍ የማታልፈውን ቤተ ክርስቲያን አንድ አድርገን፣ በጋራ ተመካክረንና ችግራችንን በውይይት ፈተን ለቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚከፈለውን ዋጋ ከፍለን፣ አንዲት፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለትውልድ ማስረከብ አለብን ብለን በእኛ በኩል ለሰላሙ ቅድሚያ ሰጥተን ነበር። "አንድ ሞኝ ያሠረውን ሰባት ብልህ አይፈታውም" እንደሚባለው ልዩነትን ለትውልድ እንዳናስተላልፍ ብለን ቅዱስ ሲኖዶስ ብዙ ጥረት አድርጓል። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ያሉት በቁጥር ያነሱ ጥቂት አባቶችም ሆኑ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አንድ እንሆን ዘንድ ፈቃደኞች አልሆኑም። በመሠረቱ አብሮ ለመሥራት ፈቃደኛነት ከሌለ ማስገደድ አይቻልም። ጌታችንም እኮ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም በእደ ዮሐንስ የተጠመቀው ቅዱስ ዮሐንስ ፈቃደኛ በመሆኑ ነበር። በማኅፀነ ድንግል ማርያምም ያደረው እመቤታችን ፈቃደኛ በመሆኗ ነበር። ስለዚህ በክርስቶስ ልደትም ሆነ በጥምቀቱ የሰው ልጅ ሁሉ የተጠየቀው ለሰላም በጎ ፈቃዱ እንዲሆን ነው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የፈቀደው ቀን እስኪመጣ ድረስ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት እየጸለይንና በመላው ዓለም የተሰደደውን ሕዝባችንን እያጽናናን ሐዋርያዊ ተልእኳችንን እናከናውናለን።

በመጨረሻም ድካማችንና አገልግሎታችን ከአምላካችን ፍጹም ዋጋ የሚያስጥ እንዲሆን ሁላችንም በቅንነትና በአንድነት አብረን እንድንሠራ መንፈሳዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ዛሬ በክርስቶስ ጥምቀት የሰማይ በር ለሁላችንም ተከፍቷልና ማንም ሊዘጋው አይችልም። ስለሆነም ቅዱስ ሲኖዶስም በተጠናከረ መልኩ ተደራጅቶ ሥራውን ይሠራል። እኔም ስደተኛው ሕይወቴ የፈቀደልኝን ያህል እየተዘዋወርኩ ልጆቼን ለመባረክ ምንጊዜም ዝግጁ ነኝ። ከዚህ በፊት እንደተናገርኩት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ከሚመራት መንፈስ ቅዱስ የተሰጠኝን መንፈሳዊ አደራ ባለሁበት ዘመን ሁሉ ለመወጣት ቃል በገባሁት መሠረት እየሠራሁ ነው።



1152 S Stone Mountain Lithonia, GA 30058 Phone: (770) 469-5462 P.O. Box 711 Stone Mountain, GA 30086

**አባ መርቆሬዎስ**
**ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ስለዚህም በመላው ዓለም የምትገኙ ካህናትና ምእመናን ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠውን መመሪያና ሕግ እየተከተላችሁ የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት አክብራችሁ እንድታስከብሩ ቤተ ክርስቲያን ጥሪዋን ታስተላልፋለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ለትውልድ ጠብቆ ለማስተላለፍ እንዲቻል ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ማክበር፣ ትምህርተ ሃይማኖትንና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን እንዲሁም ኢትዮጵያዊ ታሪክ፣ ባሕልና ትውፊትን ለልጆቻችን በትጋት ማስተማር ይኖርብናል። ይህንን መልካም ተግባር ማድረግ ደግሞ በወልድ ውሉድ፥ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙ ሁሉ ግዴታ ነው።

**እግዚአብሔር በበረከተ ጥምቀቱ በሰማያውያንና በምድራውያን በረከት ይባርካችሁ፥ ይቀድሳችሁ!**

**እግዚአብሔር አምላክ ኢትዮጵያ አገራችንን ይባርክልን፥ ይጠብቅልን፤**

**ለሕዝባችንም ፍጹም ሰላምንና አንድነትን ይስጥልን!**

አባ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ

ጥር 10ቀን 2005 ዓ.ም

**1152 S Stone Mountain Lithonia, GA 30058 Phone: (770) 469-5462 P.O. Box 711 Stone Mountain, GA 30086**

በስደታቸውም ቀብተው የሾሙአቸው ሊቃነ ጳጳሳትም ቀሳውስትን ዲያቆናትን በመሾም በመላው ዓለም ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ላይ ናቸው ። በቅድስናቸው የተመሰገኑ ፥ በሊቅነታቸው የከበሩ ፥ በስብከታቸው በመላው ዓለም ያሉ የተዋሕዶ ልጆች የሚያደንቋቸው ታላላቆቹ መምህራን ዛሬ በመላው ዓለም ተበትኖ ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን እያጽናኑት ይገኛሉ ። ይህ ሁሉ የቅዱስነታቸው የስደታቸው ፍሬ ነው።

## <u>ሕገ ወጡ ሲኖዶስ በስደት ላይ ያሉትን አባቶች በሕዝብ ፊት ለመክሰስ ይጠቅሙኛል ብሎ ባቀረባቸው የጽሑፍ መረጃዎች ላይ የተሰጠ አጭር መልስ ።</u>

***<u>መረጃ አንድ</u>*** ቅዱስ ፓትርያርኩ በወቅቱ የሀገሪቱ መሪ የነበሩትን ሰላም ሲሉ ያሚያሳይ ፎቶ ግራፍ የጠቀሱበት ምክንያት ፣ ፓትርያርኩ አስገድደውም ቢሆን መስቀል ማሳለም ነበረባቸው እንጂ ሰላም ማለት አልነበረባቸውም በማለት ቅዱስነታቸውን ለማጥላላት ታስቦ ነው ። ለዚህ የሚሆነውን መልስ በገጽ 11 ላይ መመልከት ይበቃል።

***<u>መረጃ ሁለት፡-</u>*** ነሐሴ 28/1983 ዓ/ም የቅዱስ ሲኖዶስ ቃለ ጉባኤ፡- ይህ ቃለ ጉባኤ ፓትርያርኩ ሲኖዶሱን ሰብስበው ሥልጣን ተረከቡኝ አሉ ባሉት ቀን የተያዘ ቃለ ጉባኤ አለመሆኑንና ሰብሰቢውም ፓትርያርኩ ሳይሆኑ ረዳታቸው እንደ ነበሩ ያረጋግጣል ። ነገር ግን በዚህ ፈንታ ፓትርያርኩ ሰብስበው ያነጋገሩበትን ቃለ ጉባኤ ለማቅረብ አልቻሉም ። ምክንያቱም የቅዱስ ፓትርያርኩን ፊርማ ለማሳየትና ለማሳመን ይጠቅም ነበር ። ነገር ግን ይህ ቃለ ጉባኤ ቅዱስ ፓትርያርኩ እያሉ እንደ ሌሉ ቈጥሮ ፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ላይ የወቅቱ ሲኖዶስ በክፉ እንደ መከረባቸው ሁሉ ፣ በዚህ ጊዜም እንዲሁ በመንግሥት ጫና ተገዶ ያካሄደውን ስብሰባ የሚያስታውስ እንጂ ፥ ቅዱስነታቸውን ቅዱስ ሲኖዶስ እንዳወረደ የሚናገር አይደለም ። ቅዱስነታቸውንም ለማሳሳት ፣ በሚቀርቧቸው ሰዎች በኩል ብዙ ተሞክሮ ስላልተሳካ *‹አመመኝ ወርጃለሁ ብለው ቢጽፉልን መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጽመውን በደል ሊቀንስልን ይችላል›* በሚል ወዳሉበት ፎቅ በመሄድ እንደ ጠየቁአቸው በወቅቱ የነበሩት አባቶች ያስታውሳሉ ።

የቅዱስነታቸው መልስ ግን *«ከእኔ ምን ትፈልጋላችሁ እንደ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ልታስገድሉኝ ትፈልጋላችሁን ? ... እኔ አልታመምኩም አልሠራም አላልኩም»* ብለው መልሰዋቸው ነበር ። ታዲያ ይህን ቃለ ጉባኤ ለማደናገሪያ ካልሆነ በቀር ስለ ቅዱስነታቸው በፈቃድ መውረድ ምንም መረጃ አይሰጥም ። ወረዱም አይልም ።

***<u>መረጃ ሦስት፡-</u>*** እንዲሁም በተመሳሳይ ቀን ነሐሴ 28/1983 ዓ/ም ሌላ ሁለተኛ ቃለ ጉባኤ መዘጋጀቱን ያመለክታል ። የቃለ -ጉባኤውም ፍሬ ሐሳብ *"ቅዱስ ፓትርይርኩ ስለ ታመሙ እስኪሻላቸው ድረስ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥራውን እየሠራ ይቆያል"* ይላል እንጂ አወረድን አይልም ። በዚያም ላይ ሲኖዶሱ በወቅቱ በቅዱስነታቸው ላይ በደል ፈጽሟል ፤ ለሕገ ቤተ ክርስቲያን መሻር በር ከፍቷል ። በመሆኑም ያን ስሕተት በጋራ እናርመው ቀኖናችን ለቤተ ክርስቲያን አንድነት መሠረት በመሆኑ ስሕተቱን እናርመው ነው እያልን ያለነው ። ስለዚህ መረጃው በወቅቱ ቅዱስ ሲኖዶስ መንግሥት ባሳደረበት ጫና ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን ከወያኔ ጫና ለመታደግ ሲል ታላቅ ስሕተት መሥራቱን ብቻ ነው የሚያስረዳው ። ነገር ግን የሁለቱ ቃለ ጉባኤዎች ቀን እና ዓ/ም አንድ መሆን ፥ ከሁለቱ የአንደኛው ቃለ ጉባኤ እውነተኛነት ጥያቄ የሚያስገባ ነው ።

***<u>መረጃ አራት፡-</u>*** የመስከረም 27 ቀን 1984 ዓ/ም ቃለ ጉባኤም በመንግሥት ፍራቻ ቅ/ ሲኖዶስ ቅዱስ ፓትርያርኩን ከግቢ ለማስወጣት መምከሩን ነው የሚያሳስበው ። ስለዚህ የቅዱስ ሲኖዶስን ስሕተት እየመሰከረ ይኖራል እንጂ ቅዱስ ፓትርይርኩ ይህን ስላጠፉ ይህንንም ስላጎደሉ ወረዱ የሚል የለም ።

በመጽሐፈ ሐሰታቸው ከገጽ **27-32** ያስገቡት ግን ሲኖዶሱ ከፈረሰ በኋላ አደረግነው የሚሉትን ነው ያስቀመጡት ። በዚያ ጊዜ ግን አቡነ ዜና ማርቆስም ሆኑ ሌሎች አባቶች አልነበሩበትም ፣ ከጊዜ በኋላ የገባ የሐሰት መልእክት ነው ። ስለዚህ መረጃ ሊሆን አይችልም ።

***<u>መረጃ አምስት</u>***፡- ቅዱስ ፓትርያርኩ ከመንበረ ፓትርያርኩ እንዲወጡ ስለ ተጻፈው ደብዳቤ ይዘትና ትርጉም ፣ ስለ ፓትርያርኩ ስደት በሚናገረው ክፍል ላይ ይመልከቱ ። እንደገና ለማስታወስ ቅዱስ ፓትርያርኩ ያለፈቃዳቸው ተገደው መውጣታቸውን ነው የሚያመለክተው።

***<u>መረጃ ስድስት፡-</u>*** *የብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅን ፎቶ ግራፍ በማስቀመጥ አቡነ መልከ ጼዴቅ የአባ ጳውሎስን ሢመት ተቀብለዋል ፥ በፓትርያርኩ መውረድ ተስማምተዋል ፤ለማለት ከጅለዋል ። አንደኛ ገና አቡነ ጳውሎስ ሳይሾሙ ወያኔ ሲኖዶሱን ሲያፈርስ ብፁነታቸው ተቃውመዋል ። ፓትርያርኩም ይውረዱ ሲልም አውግዘዋል ፤ በመሠረቱ ይህ ማለት ብፁነታቸው ከአባ ጳውሎስ ጋር ግላዊ ጥላቻ ነበራቸው ማለት አይደለም ። ስለዚህ ይህ ፎቶ የብፁነታቸውን ስምምነት አያመለክትም ።*

## *<u>የእርቁን ሂደት ያደናቀፈው የሰላምንስ በር የዘጋ ማን ነው ?</u>*

*ሕገ ወጡ ሲኖዶስ በስደት ያሉትን አባቶች እና በአገር ቤት ያሉትን ለማቀራረብ ደፋ ቀና የሚሉትን የሰላም ልዑካን ከመንግሥት ጋር ተመሣጥሮ ከአገር ማሳደድ ብቻ ሳይሆን ፥ የሐሰት ክስ በማቀነባበር እንደ ተለመደው በሐሰት መክሰሱ የሚዘነጋ አይደለም ። ይኸው አካል በሰላም ልዑካኑ በኩል የተስማማበትን ቃል በማጠፍ የሰላሙን በር ከዘጋ በኋላ ፥ አሁንም ያለምንም ኀፍረት ፥ ሰላሙን እምቢ ያሉት በውጭ ያሉት አባቶች ናቸው በማለት ለመጻፍ ደፍሮአል ። ይህ ዓይነቱ ቅጥፈት የሂትለር ፕሮፓጋንዳ ኃላፊ የነበረው ጎብልስ እንኳ ያልሞከረው ቅጥፈት ነው ። በዓለም ፊት አስታራቂዎቹን አዋክቦ የሰደደው አካል ፥ የእርቁ ጉባኤ ሳያልቅ የራሱን ውሳኔ ለመገናኛ አካላት የላከው አካል ፥ ኃላፊነቱን በስደት ባሉት አባቶች ላይ አድርጎአል ።ዓለም ሁሉ በተለያዩ ሚዲያዎች የተከታተለውን እውነት ፥ የአደራዳሪው የሰላምና አንድነት ጉባኤ አባላት የመሰከሩትን አጥቁሮ በሐሰት ከጻፈ ፥ የዛሬ 21 ዓመት የፈጸመውን ስሕተት አጽድቆ በመጻፍ የዛሬውን ትውልድ ግራ ቢያጋባ ምን ይደንቃል? ለማንኛውም የታሪክ ምስክር እንዲሆን አስታራቂው አካል በመጨረሻ በታላቅ ኀዘን ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ያስተላለፈው መግለጫ በሚቀጥሉት ገፆች ላይ ተቀምጧል ።*

*ከዚህ በታች ለመረጃነት የቀረበውን መግለጫ አንብቦ የተረዳ አእምሮ የሰላሙን በር ማን እንደ ዘጋ በቀላሉ ሊረዳ ይችላል ። ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ ።*

*ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከዚህ በፊት ለምእመናን እንዳሳወቀው ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ተገቢውን ጥረት አድርጎ ነበር ። በስደት የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ «ስለ ፍቅር በስማም ይቅር» የሚለውን የሰይጣን ምክር አይቀበለውም ። የአንድነታችን ምንጩ እውነታችን ነው ። ማለትም የፈረሰው ቀኖና እንደ ፈረሰ እንታረቅ ፤ ወደ እኛ ግቡና ቤተ ክርስቲያናችሁን ለማፍረስ ታጥቆ ለተነሣው ኃይል አገልጋይ ሁኑለት ፥ በሕዝቡ ላይ የሚፈጽመውን ግፍና ተንኮል በማንሣት መንግሥትን አትውቀሱ የሚለውን ብሂል ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አይቀበለውም ።*

*ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት የሚያስጠብቅ አንድነቷን የሚመልስና የሚያጸና እውነተኛ በሆነ ነገር ላይ የተመሠረተ የሰላምን መንገድ ለማስተናገድ የቅዱስ ሲኖዶስ በሮች ምንጊዜም ክፍት ናቸው ።*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰላምና አንድነት ጉባኤ
Council of Peace and Unity of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
"የተረፈውንም ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው" (፪ ቆሮ ፲፩፥፳፰)

የካቲት 12/2005 ዓ.ም

Feb 19/2013

## በወቅታዊው የቤተ ክርስቲያናችን ጉዳይ ላይ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ የተሰጠ መግለጫ።

### የመግለጫው ምክንያት፡-

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ላለፉት ሦስት ዓመታት በአገር ቤትና በውጭው ዓለም የሚገኙ አባቶችን በማስማማት ቤተ ክርስቲያንን አንድ ለማድረግ ያደረገውን ከፍተኛ ጥረት በዝርዝር ለመግለጽና የዕርቁ ሒደት ምን ይመስል እንደነበር በኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም ለሚኖሩ መላው ኦርቶዶክሳውያን ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት መዘምርን እንዲያውቁት ለመግለጽ ነው። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ የማስታረቅ ሥራውን የጀመረው በኢትዮጵያ በኩል በብፁዕ ወቅዱስ ዶ/ር አቡነ ጳውሎስ ፊርማ በተጻፈ ደብዳቤ፤ በውጭም በኩል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ መልካም ፈቃድ በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ፊርማ በተጻፈ ደብዳቤ ነው። የሰላምና አንድነት ጉባኤው በርካታ ምእመናንና አብያተ ክርስቲያናት የገንዘብ ድጋፍ እያደረጉለት ሦስት ጉባኤያትን በማዘጋጀት አባቶች ችግሮቻቸውን በጋራ ተነጋግረው በውይይት እንዲፈቱ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል። በእያንዳንዱ ጉባኤ ላይም አለመግባባት በተፈጠረባቸው ሐሳቦች ላይ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ለዕርቀ ሰላሙ ሥምረት ይበጃል ያለውን የመፍትሔ ሐሳብ እያቀረበ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት አቅም የፈቀደውን ያህል የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ እስካሁን ያካሔዳቸውን ሦስቱን የዕርቀ ሰላም ውይይቶች አጠቃላይ ገጽታና ሒደት ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እናቀርባለን።

### የመጀመሪያው ጉባኤ

ይህ የመጀመሪያ ጉባኤ የተካሔደው ከሐምሌ 26-28, 2002 ዓ.ም በሰሜን አሜሪካ ቨርጂኒያ ግዛት ማክሊን ሆቴል ሲሆን ከኢትዮጵያና ከውጭው ዓለም የተወከሉ አባቶች እንዲገናኙ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረጉ ይታወሳል። ይሁን እንጂ ለዚህ ጉባኤ አለመሳካት ትልቁ ምክንያት ከኢትዮጵያ በኩል ልዑካን ከመሰየማቸው አስቀድሞ በውጭ ካሉት አባቶች ለሰላምና አንድነት ጉባኤው የቀረበ ጥያቄ ነበር። ይኸውም በኢትዮጵያ

P. O. BOX 505, Stone Mountain, GA 30086 E-mail: copauoeotc@yahoo.com

በኩል በልዑክነት ከተመደቡት ከአንዱ ጋር ከባድ ቅሬታ ስላለን አብረን ቤተ ክርስቲያንን አንድ ለማድረግ የሚያስችል ልባዊ ንግግር ለማድረግ ስለምንቸገር በሌላ ሰው እንዲለወጡ ይደረግልን የሚል ነበር። ይሁን እንጂ ጉባኤው ወደ አዲስ አበባ ደውሎ ለመጠየቅ ከልዑካኑ መሪ ጋር በተነጋገረበት ጊዜ «እኛ የምንመጣው ትልቁን ችግር ልንፈታ ስለሆነ ችግር የለም፤ ስንመጣ እዚያው እንፈታዋለን» የሚል ምላሽ ተሰጠን። ከኢትዮጵያም ሆነ ከውጪው ዓለም የተወከሉት አባቶች ስብሰባው ቦታ እንደተገኙ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ከስብሰባ በፊት ልዑኩን በውጪ ካሉት አባቶች ጋር ያለባቸውን ችግር በመፍታት ወደ ዋናው ድርድር ለመግባት ጥረት ሲያደርግ ከአዲስ አበባ የመጡት ልዑካን ጸሐፊ «ከመመሪያ ውጭ ያደርገናል፤ አይሆንም አሉ።» በወቅቱ ለሰጡት መልስ ያቀረቡት ምክንያት "በጋራ እንድንነጋገር እንጂ በግል ይቅርታ ልንጠያየቅ አልመጣንም" የሚል ነበር። የሰላምና አንድነት ጉባኤው ቀደም ሲል በውጭ ያሉት አባቶች ባቀረቡለት ጥያቄና ጉባኤውም በገባው ቃል መሠረት ልዑኩ ይቅርታ እንዲጠይቁ ያደረገው ጥረት ባለመሳካቱ ምክንያት ጉባኤው ሁለቱንም ወገኖች በእንባ ጭምር ቢለምንም የሚሰማ ባለመገኘቱ የመጨረሻ እንደ መፍትሔ አድርጎ ያቀረበው ከኢትዮጵያም ከውጭውም ዓለም የመጡት አባቶች ሊቃውንቱ ቀርተው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በሆኑት በሊቃነ ጳጳሳት ደረጃ ብቻ ተነጋገሩ የሚል ሲሆን ይህም ተቀባይነት አላገኘም። ይሁን እንጂ ልዑካኑ ፊት ለፊት ተገናኝተው ባይነጋገሩም ሁለቱም አባቶች በሰላምና አንድነት ጉባኤው አማካኝነት በተዘዋዋሪ መልኩ እንዲደራደሩ ተደርጓል። በዚህም ለወደፊቱ ግንኙነት እንቅፋት የሚሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ተስተካክለው የሰላሙ ጉባኤ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተስማምተው ነበር።

**<u>ሁለተኛው ጉባኤ</u>**

ሁለተኛው ጉባኤ ከየካቲት 2-11 ቀን 2004 ዓ.ም በአሜሪካ ፊኒክስ፤ አሪዞና ከተማ የተካሔደ ሲሆን ከ20 የልዩነት ዓመታት በኋላ አባቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ፊት ለፊት ተገናኝተው ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ተነጋግረው በአንድነት የጋራ መግለጫ ማውጣታቸው ይታወሳል። በዚህ ጉባኤ ላይ በዋነኛነት ቀርበው የነበሩት የመነጋገሪያ አጀንዳዎች፡-

1ኛ/ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት፤

2ኛ/ አራተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን በተመለከተ ነበር።

በውይይቱ ወቅት በሰሜን አሜሪካ ያሉት አባቶች ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከመንበራቸው የወረዱት ተገድደው ነው፤ አቡነ ጳውሎስም አራተኛው ፓትርያሪክ በሕይወት እያሉ በመሾማቸው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፈርሷል። ስለዚህ የፈረሰውን ቀኖና ለማረምና ለማደስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ወደ መንበራቸው መመለስ አለባቸው የሚል ነበር። ከኢትዮጵያ የመጡት ልዑካን ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሥልጣናቸውን ራሳቸው ለቅዱስ ሲኖዶስ "አልችልም፥ አሞኛል" ብለው ስላስረከቡ ጉዳዩ በምልዓተ ጉባኤ ተወስኖ እርሳቸው ከሥልጣናቸው ከወረዱ በኋላ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት አምስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የተሾሙ ስለሆነ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አልፈረሰም። ይልቁንም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሌለ ስደተኛ ሲኖዶስ አቋቋምን በማለት ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያፈረሳችሁ እናንተ ናችሁ ብለዋል።

2

አያይዘውም "አራተኛው ፓትርያርክ ቅዱስ ሲኖዶስ ከዚህ ቀደም በወሰነው መሠረት ቅዱስነታቸው በፈቀዱት ቦታ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ተሟልቶላቸው ይኑሩ፤ ለሾሟቸው ጳጳሳትም ሀገረ ስብከት ይሰጣቸዋል" ብለዋል።

የሰላምና አንድነት ጉባኤው የሁለቱንም አካላት ሐሳብ በሚገባ ካዳመጠ በኋላ አባቶች ይበልጥ በሚያቀራርባቸውና ወደ አንድነት በሚያመጣቸው ሐሳብ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ብርቱ ጥረት አድርጓል። በዚህ መሠረት ለሃያ ዓመታት የቆየውን ችግር በቀላሉ መፍታት ባይቻልም ውይይቱ በመደማመጥና በመከባበር ሊቀጥል ችሏል። ስለሆነም የአሪዞናው ዕርቀ ሰላም ጉባኤ "ጽኑ የሰላም መሠረት የተጣለበት ጉባኤ ነው" ብለው የጋራ መግለጫ ያወጡበትና ቀጣይ ስብሰባ እንዲዘጋጅ ተስማምተው የወሰኑበት ጉባኤ ሆኖ ተጠናቅቋል። የሰላምና አንድነት ጉባኤውም ከውይይቱ ያጠናቸውን ነገሮች መነሻ በማድረግ ባለ ሰባት ነጥብ የመፍትሔ ሐሳብ ለሁለቱም ወገን በጹሑፍ አቀርቧል። ለዚህም ልዑካን ሰይሞም ወደ ሁለቱም ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በመላክ ጉዳዩን በጥንቃቄ እንዲያስረዱ አድርጓል። በአሪዞናው ጉባኤ ላይ በተደረሰው የጋራ ስምምነት መሠረት መሠረት ሦስተኛው የዕርቀ ሰላም ድርድር ጉባኤ ዝግጅት ቀጠለ። ይህ በዚህ እንዳለ ግን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ድንገተኛ ዕረፍት መሰማቱ አሳዛኝና አስደንጋጭ ነበር። ስለሆነም የሰላምና አንድነት ጉባኤው በወቅቱ ልዑካንን ልኮ በቅዱስነታቸው ሥርዓተ ቀብር ተገኝተው የጉባኤውን የኃዘን መግለጫ መልእክት እንዲያሰሙ አድርጓል። በዚህም የዕርቀ ሰላሙ ጥረት ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና በአፋጣኝ ለፍጻሜ እንዲበቃም ለቅዱስ ሲኖዶስ ጥያቄውን  አቅርቧል።

<u>ሦስተኛው ጉባኤ</u>

በመሠረቱ የሰላምና አንድነት ጉባኤው አንዱን ችግር አሳለፍኩ አሁንስ ሰላም ይገኛል ብሎ ተስፋ ሲያደርግ ሌላ ያልታሰበ ችግር ከፊቱ ይደቀንበታል። ይሁን እንጂ በየጊዜው የሚከሰተውን ችግር ፈትቶ ሂደቱን መልክ ለማስያዝ የሚጠይቀው ጊዜና ድካም ቀላል አልነበረም። በዚህም ሁኔታ ሦስተኛውን ዙር ጉባኤ ከኅዳር 26-30 ቀን 2005 ዓ.ም (Dec. 5-9, 2012) በዳላስ፤ ቴክሳስ ለማካሔድ ተቻለ። ይህ ጉባኤ ከዚህ ቀደም ካሳለፍናቸው ሁለት ጉባኤያት እጅግ በተለየ መልኩ የመቀራረብና የመከባበር መንፈስ የታየበት ልዑካኑ ገና እንደተገናኙ የፍቅር ሰላምታ የተለዋወጡበት ነበር። በጉባኤው ዋዜማ በዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ደማቅ አቀባበል ከተደረገላቸው በኋላ በአንድ ቤተ መቅደስ ውስጥ ተገኝተው ጸሎተ ኪዳን በጋራ አድርሰዋል። ከሕዝቡ የተደረገላቸውን የአቀባበል ሥነ ሥርዓት በእጅጉ አድንቀውና አመስግነው በደስታ ተቀብለውታል። ጉባኤው ሲጀመርም የጉባኤውን መክፈቻ ጸሎት "እርስዎ ይጀምሩ" "የለም እርስዎ ይጀምሩ" እየተባባሉ በፍቅር በመገባበዝ ጀምረውታል።

በውይይቱም ወቅት ሁለቱም ወገኖች ከላካቸው አካል ይዘውት የመጡትን መሠረተ ሐሳብ በሰፊው ተነጋግረውበታል። ይኸውም የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ወደ አገራቸው መመለስ ለዕርቀ ሰላሙ ስኬታማነት ዋነኛ መሠረት መሆኑን በጋራ የተስማሙበት ቢሆንም በሁለቱም ወገን ቅዱስነታቸው እንዴትና በምን ሁኔታ ይመለሱ በሚለው ዐቢይ ጉዳይ ላይ የአቋም ልዩነት ታይቷል። ስለሆነም በኢትዮጵያ ልዑካን በኩል የቀረበው ዋና ሐሳብ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ወደ ቅድስት አገራቸው ገብተው፣ ክብራቸው ተጠብቆና የሚያስፈልጋቸው

ሁሉ ተሚልቶላቸው እርሳቸው በፈለጉት ቦታ ይኑሩ" የሚል ነው። አያይዘውም ምክያቱን ሲገልጹ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ወደ መንበራቸው ቢመለሱ ታሪክ ይፋለስብናል" የሚል ነበር። በአንጻሩ ደግሞ በውጭ አገር ያሉት ልዑካን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ሲባል "ቅዱስነታቸው ከነሙሉ ሥልጣናቸው ወደ መንበራቸው መመለስ አለባቸው፤ ፓትርያርክ እያለ ሌላ ፓትርያርክ መሾም ሥርዓት አልበኝነትን ያስከትላል" ብለዋል። ምክንያቱም «ቅዱስነታቸውን ወደ መንበራቸው እንዳይመለሱ የሚያደርጋቸው ቀኖናዊ በደል ስለሌለባቸውና በአሁኑ ጊዜም መንበሩ ክፍት ስለሆነ ሊመለሱ ይገባል» ብለዋል።

ስለዚህ ልዑካኑ ልዩነት በታየባቸው መሠረታዊ ሐሳቦች ላይ "አሁን በራሳችን ለመወሰን ከአቅማችን በላይ በመሆኑ ሰይሞ ወደላከን አካል ተመልሰን ጉዳዩን በሰፋት አስረድተን እንደገና የምንገናኝበትና የዕርቀ ሰላሙን ውይይት የመጨረሻ ምዕራፍ የምናደርስበት ቀጣይ አራተኛ ጉባኤ በቅርቡ ያስፈልገናል" ሲሉ ለሰላምና አንድነት ጉባኤው ሐሳባቸውን አቅርበዋል። ጉባኤው ከልዑካኑ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት አራተኛው ጉባኤ ከጥር 16-18 ቀን 2005 ዓ.ም (Jan. 24-26/2013) በሎስ አንጀለስ፤ ካሊፎርኒያ እንዲካሔድ ሐሳብ አቅርቧል። የሰላምና አንድነት ጉባኤው ያቀረበውን ሐሳብ የሁለቱም ወገን ልዑካን በአንድ ድምፅ ተቀብለው ተስማምተውበታል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ የግራ ቀኙን ፍሬ ሐሳብ በጥሞና አዳምጦና በጉዳዩ ላይም በስፋት ተወያይቶ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ሥምረት ይበጃል ብሎ ያመነበትን ባለ አራት ነጥብ የመፍትሔ ሐሳብ ለልዑካኑ በጽሑፍ አቅርቦ በንባብ አሰምቷል። ለልዑካኑ ያቀረበውን የመፍትሔ ሐሳብም በልዑካኑ ስምምነት መሠረት ለሁለቱም ሲኖዶሶች ምልዓተ ጉባኤ በደብዳቤ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቦ ነበር።

__የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ያቀረበው የመፍትሔ ሐሳብ።__

1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን አስመልክቶ ከምንም በላይ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ሲባል ቅዱስነታቸው ወደ መንበራቸው ተመልሰው በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተጠንቶ በሚጸድቀው የጋራ መመሪያ መሠረት የቤተ ክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ ተግባራት ብቻ እንዲያከናውኑ ቢደረግ፤
2. የቤተ ክርስቲያኒቱን የአስተዳደር ዘርፍ በተመለከተ ደግሞ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተጠንቶ በሚወጣው መመሪያ መሠረት በኢትዮጵያ ከሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል በሚመረጥ እንደራሴ ወይም በጋራ ስምምነት በሚሰየም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲመራ ቢደረግ፤
3. ከላይ የተገለጸውን የመፍትሔ ሐሳብ ከጠቅላላው የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ አንጻር ለማገናዘብ እንዲቻል የዐራተኛውና የአምስተኛው ዘመነ ፕትርክና እንደ ተጠበቀ ሆኖ በየጊዜው የተከናወኑትን ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተግባራትንም ሙሉ በሙሉ አክብሮ በመቀበል በዕርቀ ሰላሙ አማካይነት የቤተ ክርስቲያናችንን የታሪክ ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚቻል በመሆኑ፤
4. ከዚህም ጋር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በኋላ በጋራ የሚሾመውን ቀጣይ ፓትርያርክ ስድስተኛ

4

ፓትርያርክ አድርጎ በመሰየም የታሪክ ሒደቱ እንደተጠበቀ ሆኖ እንዲቀጥል ቢደረግ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ሊሰጥ ይችላል ብሎ ጉባኤው ያምናል።

5. በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያናችን በከባድ ችግር ውስጥ መሆኗንና ዕርቀ ሰላሙ የቅዱስ ሲኖዶስ ተቀዳሚ አጀንዳ መሆን እንደሚገባው ይታመናል። ስለሆነም ለሦስት ዓመታት ሲካሔድ የቆየው የዕርቀ ሰላም ንግግር ለሠመረ ውጤት እንዲበቃና ሃያ አንድ ዓመታትን ያስቆጠረው አሳዛኝ የልዩነት ታሪክ በአንድነት እንዲተካ፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን በጥልቀት ተመልክቶ ለዕርቀ ሰላሙ የመጨረሻ እልባት መስጠት ወቅቱ የሚጠይቀው ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ኃላፊነት መሆኑን የሰላምና አንድነት ጉባኤው በጽኑ ያምናል።

**<u>በእንጥጥል ላይ እንዳለ ሳይቋጭ የቀረው የአራተኛው ዙር ጉባኤ እንቅፋቶችና የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዕርቀ ሰላም ሒደት እንዳይሳካ ያደረጉት ዋና ዋና ምክንያቶች፤</u>**

1. በኢትዮጵያ ያሉ አንዳንድ አባቶች ከቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ይልቅ ለሢመተ ፓትርያርክ ቅድሚያ በመስጠታቸውና የላኳቸውን ልዑካን ሪፓርት ሳይሰሙ አስመራጭ ኮሚቴ መሰየማቸው፤
2. የኢ/አ/ተ/ቤ/ክ የሰላምና አንድነት ጉባኤ አባላት በልዑካኑ የስምምነት ውሳኔ መሠረት ወደ አዲስ አበባ ቅዱስ ሲኖዶስ ተሰይመው ከሔዱ በኋላ የተላኩበትን ዐቢይ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዳያቀርቡ እስካሁን ድረስ እንኳን ማንነታቸው ባልታወቀና ባልተረጋገጠ ግለሰቦች ተላለፈ በተባለ ሕገ ወጥ ትእዛዝ ወደ መንበረ ፓትርያርኩ ቅጽረ ግቢ እንዳይገቡ በጥበቃ ሠራተኞች መከልከላቸው፤
3. ከዚህም በላይ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ አንደኛውን ልዑክ ካለአንዳች ምክንያት በግዳጅ ከሀገር እንዲወጡ መደረጉ፤ ሁለተኛውንም ልዑክ በማጉላላትና ወደ ቤተ ክህነት ግቢ እንዳይገቡ በማገድ፤ በቀጠሮ እንኳን ለሚጠብቃቸው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ከላይ የዘረዘርናቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች የያዘውን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ደብዳቤ አቅርበው እንዳያስረዱና ቅዱስ ሲኖዶስ በጉዳዩ እንዳይመክርበት መደረጉ፤
4. ገና ከጅምሩ ጀምሮ ዕርቀ ሰላሙን የማይፈልጉና በግልጽ ይቃወሙ የነበሩ አንዳንድ አባቶች ፈጽሞ የተዛባና ከእውነት የራቀ መሠረተ ቢስ መረጃ ለመንግሥት ባለሥልጣናትም ሆነ ለኅብረተሰቡ መስጠታቸው፤
5. በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ፍጹም ሰላምና አንድነት እንዲሰፍን ለማድረግ ላለፉት ሦስት ዓመታት ሲካሔድ የቆየው የዕርቀ ሰላም ጥረት ከዳር እንዲደርስ በማይፈልጉ ጥቂት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አማካይነት ቅዱስ ሲኖዶስ እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ የተጀመረው የዕርቀ ሰላም ውይይት ለውጤት እንዲበቃ ባለማድረጉ ምክንያት መንግሥት በቅዱስ ሲኖዶስ ሉዓላዊ ሥልጣን ላይ ግልጽ ተጽእኖና ጫና በማድረጉ፤
6. በመጨረሻም ጥር 8 ቀን 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ ስድስተኛ ፓትርያርክ ለመሾም በችኮላ መወሰኑ የሰላሙን በር ከመዝጋቱም በላይ የዕርቀ ሰላሙን ውጤት በጸሎትና በታላቅ ተስፋ ሲጠባበቅ ለቆየው መላው ሕዝበ ክርስቲያን ታላቅ መርዶ ሆኗል።

በዚህ አጋጣሚ በብፁዕ ወቅዱስ ዶ/ር አቡነ ጳውሎስ አባታዊ ቡራኬና በቅዱስነታቸው በሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ መልካም ፈቃድ እንዲሁም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አባታዊ ቡራኬና

በቅዱስነታቸው በሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ መልካም ፈቃድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ የዕርቀ ሰላሙን ጥረት እንዲያካሒድ በመደረጉ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ከዚህም ጋር ጉባኤው በጠየቀው መሠረት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መመሪያ ሰጪነት ቅዱስ ሲኖዶስ ለሁለት ጊዜያት የልዑካኑን የአየር ቲኬት በመሸፈን ስላደረገልን ከፍተኛ ትብብር ጉባኤው ከልብ ያመሰግናል። በአጠቃላይ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ባለፉት ሦስት ዓመታት ባደረገው የዕርቀ ሰላም ጥረት በጸሎታችሁ፣ በሐሳባችሁ፣ በምክራችሁ፣ በገንዘባችሁና በጉልበታችሁ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ላደረጋችሁልን አብያተ ክርስቲያናት፣ ምእመናን፣ ማኅበራትና ድርጅቶች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አምላክ ዋጋችሁን አብዝቶ ይክፈላችሁ እንላለን። አሁንም ስለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት የተለመደውን ትብራራችሁንና ድጋፋችሁን እንዳታቋርጡ በአክብሮት እናሳስባለን።

ይልቁንም ከኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ የሰላም ልዑካን ሆነው የመጡ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በልዑካኑ ጸሐፊ አማካኝነት የሚደርስባቸውን ከፍተኛ ጫና ተቋቁመው ለዕርቀ ሰላሙ አጠቃላይ ሒደት ላደረጉት ያላሰለሰ ጥረት እንዲሁም በውጭ ሀገር ያሉት አባቶች ለዕርቀ ሰላሙ ሒደት ስላደረጉት ቀና ትብብር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል። ምንም እንኳን በጥቂት አባቶች አቀነባባሪነት የሰላምና አንድነቱ በር ለጊዜው የተዘጋ ቢመስልም የቤተ ክርስቲያን አምላክ እግዚአብሔር በጥበቡ ከፍቶ የቤተ ክርስቲያናችንን አንድነት እንደሚያሳየን ተስፋ እናደርጋለን። እነሆ በእግዚአብሔርም ሆነ በሰዎች ዘንድ በግልጽ እንደሚታወቀው ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ስንል እስካሁን ድረስ አቅማችን በፈቀደው ሁሉ የሚቻለንን ያህል ጥረናል። ይሁን እንጂ "ፈደዩኒ እኪተ ህየንተ ሠናይት" እንደተባለው የሰላምና አንድነት ጉባኤው አባላት ፍጹም ሰላማውያን መሆናቸው እየታወቀ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት አብዝቶ መድከም እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ብዙ እንግልት ደርሶባቸዋል።

እንደሚታወቀው የዕርቀ ሰላሙን ሒደት ለማሰናከል የፈለጉ ጥቂት አባቶችና "የቤተ ክርስቲያን" ባለሥልጣናት የሆኑ ግለሰቦች ለመንግሥት አካላት የተዘባ መረጃ በመስጠት የሰላም ልዑካኑ ከሀገር በግዳጅ እንዲወጡና እንዲጉላሉ ተደርጓል። ከዚህም ጋር በሰላም ልዑካኑ ስም ከሰላሙ በቀር አንዳችም አጀንዳ የሌለውን ጉባኤያችንን የማይወክል የሐሰት ወረቀት በመበተን ያለስማቸው ስም ለመስጠት ተሞክሯል። ለዚህ ሁሉ ግን የቤተ ክርስቲያን አምላክ ራሱ በጊዜው እንደሚመልስና እንደሚፈርድ ወደፊትም ታሪክ እንደሚያስታውሰው ስለምናምን ሁሉንም በአኰቴት እንቀበለዋለን። ነገር ግን ትናንትም፣ ዛሬም ነገም እጅግ የሚያሳስበን የቤተ ክርስቲያናችን ጉዳይ ነው። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ለመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና መምህራን፣ መዘምራንና ወጣቶች በግልጽ ለማሳወቅና በአጽንዖት ለማሳሰብ የሚፈልገው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት እስኪመጣ ድረስ ከመላው ሕዝበ ክርስቲያን ጋር በመሆን እስከ መጨረሻው ጥረቱን የሚቀጥል መሆኑን በአጽንዖት እንገልጻለን።

**እግዚአብሔር አምላክ የቤተ ክርስቲያናችንን የሰላምና አንድነት ዘመን እንዲመልስልን ተግተን እንጸልይ።**

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ።**

6

# ***መደምደሚያ***

ከላይ በተደጋጋሚ እንዳልነው ፥ የአዲስ አበባው አካል ይህን ሁሉ የሐሰት ምስክርነት የሚያትትበት ምክንያት ራሱን ከሕሊና ክስ ዝም ለማሰኘት አይደለም ። ሕሊናው ሙቶአልና ። ዋና ዓላማው ሕዝበ ክርስቲያንን በተደጋገመ ሐሰት ለማሳሳት ነው ።

አባ ማትያስም ሆኑ የቀድሞው አባ ጳውሎስ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ቤተ ክርስቲያንን በኃይል የያዙ ስለ ሆኑ ቤተ ክርስቲያን አትቀበላቸውም ። የያዙት መንበርም በወያኔ ኢሕአዴግ የተሰጣቸው እንጂ መንፈስ ቅዱስ የሰጣቸው አይደለም ። አባ ገብረ መድኅን ወደ ፓትርያርክነት እንዴት መጡ ? የሚለውን አጠር አድርጎ መልስ የሚሰጠን በወቅቱ ሰፊ ተነባቢነት የነበረው የጦቢያ መጽሔት ዘገባ ነው ። *«የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአምስተኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት ሐምሌ አምስት ቀን 1984 ተፈጽሟል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ለአሥር ዓመታት በስደት ይኖሩበት ከነበረው ከዩናይትድ ስቴት እንደ ቱሪስት ለሽርሽር አገራቸውን ሊያዩ መጥተው አምስተኛው ፓትርያርክ ሆነው ተሹመዋል»* ይላል ።

ነገሩ እውነት ነው ። ምክንያቱም እኒህ ተሿሚ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ ለአሥር ዓመት አይታወቁም ነበር ። የጦቢያ መጽሔት ጋዜጠኛ በዚሁ እትም ከእርሳቸው ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጎ ነበር ። በመጠይቁ ውስጥ እርሰዎ የሲኖዶስ አባል አልነበሩም አሁን እንዴት ፓትርያርክ ለመሆን ቻሉ ? የሚል ጥያቄ ጠይቆ ነበር ። መልሳቸው *«የነበረው ሲኖዶስ የደርግ ሲኖዶስ ስለ ነበር አልቀበለውም ነበር»* የሚል ነበር ። በእርሳቸው አባባል በደርግ ጊዜ ሲኖዶስ አልነበረም ማለት ነው ። ይህን የሐሰት መጽሐፍ የበተነው የአዲስ አበባው ሲኖዶስ የራሱን ህልውና እንኳ የማይቀበሉ ሰው ሹሞ ነው ቀኖናዊ ናቸው የሚለው ።

ምን ስላሟሉ ተመደቡ ለሚለው ያለፈውን ከመጥቀስ ያሁኑን ማስረጃ ማቅረቡ በቂ ነው ። ዋናው ቁም ነገር ትግርኛ ቋንቋ መናገርና ከአድዋ መወለድ ይሆናል ። ለዚህም ጠባብነት የተሀትን የጠባብነት ዶክትሪን ከዶክተር አረጋዊ በርሄ መጽሐፍ ላይ መመልከት በቂ ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማፈራረስ ቤተ ክርስቲያኒቱን በእርሱ ቊጥጥር ሥር ማድረግ ነበረበት ። ይህ ማለት ቤተ ክርቲያኒቱ ያላትን አገራዊነት ከሥሩ ነቅሎ በመጣል ፥ በሕዝቡ ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የምትጫወተውን ሚና በማዳከም ፥ በቋንቋ-መር ብሔርተኝነት ዶክትሪን ሥር እንድትወድቅ ማድረግ ነበረ ። ይህን የቋንቋ ዶክትሪን በሥራ ለማዋል የእነርሱ ምልምሎች የሆኑ ካህናትን ሳይቀር ያሳተፈ ሥልጠና አዘጋጅተዋል ። የቅድስት ሥላሴ ኮሌጅ ምሩቅ በሆነው ኪዳኔ ደስታና በአቶ ስብሐት ነጋ መሪነት ነበር ይህ ተልእኮ ይካሄድ የነበረው ። የሥልጠናውም ዋና ዓላማ

<u>አንድ</u> የትግራይን ገዳማትና አድባራትን አገር አቀፋዊውን አስተሳሰብ አስለቅቆ ፣ በጠባብ የዘረኝነት አእምሮ እንዲወሰኑ ማድረግ ፥ ወደ ፊትም በሚመጣው መንግሥት አመራር ይህ ዘር- ተኮር አመለካከት እንዲሰርፅ ማድረግ ነው ።

<u>ሁለት</u> ቤተ ክርስቲያንን ከዋናው መሥሪያ ቤት ለይቶ በቲፒኤልኤፍ ሥር የምትተዳደር የትግራይን ብሔርተኝነት የምታንጸባርቅ ወያኔያዊ ቤተ ክህነት መፍጠር የሚል ነበር ። በነገራችን ላይ በዚህ ሥራቸው ምን ያህል እንደ ተሳካላቸው የምናየው ፥ ሰሞኑን በቅርቡ የሞቱት አባ ጳውሎስ የተዉላቸውን ሕገ ወጥ መንበር ለመያዝ የነበረውን ሽኩቻ በዋናነት የሚመሩት አባ ማትያስና አባ ሳሙኤል ነበሩ ። ሌሎች ግን እንኳን ሊይዙት ሊያስቡትም አይችሉም ። እንግዲህ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነች ቤተ መንግሥቱ ከወያኔ ካድሬዎች ውጭ መኖር እንዳትችል እቅድ እንደ ወጣ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ ተረከዋል ። የአዲስ አበባው ሲኖዶስም ዋና ሥራው ይህን ወያኔ በረሃ ሳለ ያወጣውን አጥፊ እቅድ ማስፈጸም ነው ። የአባ ገብረ መድኅን ሹመትም ያሟላው ቀኖናውን ሳይሆን የወያኔን ቋንቋ ተኮር ዶክተሪን ነው ።

ከአሁን ቀደም <u>«የማይገለጥ የተከደነ የለም»</u> በሚል ርእስ ባወጣነው መጽሐፍ እንደ ተገለጠው እንዲሁም ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ባወጡት ‹ቋሚ ምስክርነት» በተባለው መጽሐፋቸው እንደ ገለጡት ። የሞቱት አባ ጳውሎስ ቀኖናዊ ፓትርያርክ አልነበሩም ። የተሾሙት ትውፊታዊ ቀኖናን አሟልተው ሳይሆን የወያኔ ኢህዲግን ቋንቋ ተኮር የጎሣ ዶክተሪን አምነው ስለ ተቀበሉ ነበር ።

የአባ ማትያስም ከዚህ የተለየ አይደለም ። እንዲያውም በብዙ መንገድ የከፋ ነው ። ያወገዛቸው ሲኖዶስ ውግዘቱን ሳያነሳላቸው ፥ በመገኛ ብዙኃን ያስተላለፈውን ሳይሽርላቸው ነው ሲኖዶሱን የተቀላቀሉት ። ለምን የቀቡአቸውን ፓትርያርክ ካዱ ብለን ስንጠይቅ ብዙ ጉድ ስላለው እዚህ ላይ አናነሣውም ። ከሁሉ የሚያሳዝነው ፥ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከደው ፥ ጵጵስናቸውንም በሾሙአቸው አባት ተቀምተው ሌላ ሰው በምትካቸው ተሹሞ ፥ እንደ ሌሉ ተቈጥረው የኖሩትን ሰው ፓትርያርክ ብሎ መሰየም ለቤተ ክርስቲያን ኀፍረት ነው ። ሆኖም ሹመቱ ከወያኔ ስለ ሆነና ለባለሟሎቹ በልካቸው

የተሰፋላቸው ስለ ሆነ አይደንቅም ። በወያኔ ኢሕአዴግ ቡራኬና ፈቃድ ሹመቱንስ ይቀበሉት ። የሚያሳዝነው መወገዜንም አላውቅም ብለው መናገራቸው ነው ። በዚህም የተሿሚውንና የሿሚውን ምንነት ለመገንዘብ ይቻላል ። ሊታወቅ የሚገባው ዋና ነገር አባ ማትያስም ሆኑ የቀድሞው አባ ጳውሎስ እንዲሁም የመግሥትን ሹመት አጽዳቂው የአዲስ አባባው ሲኖዶስ ሕገ ወጦች መሆናቸውን ነው ። በወያኔ ፈቃድ ካልሆነ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ስላልተሾሙ ፥ መቸም ቢሆን ሕጋዊ ሊሆኑ አይችሉም ። በአንጻሩ ስደተኛው ሲኖዶስ ሲኖዶሳዊ ቀኖናን ተከትሎ የአዲስ አበባው አካል በግፍ ከመንበራቸው ያሳደዳቸውንና ሕጋዊውን ፓትርያርክ በቤተ ክርስቲያን መሪነት ተቀብሎ በእርሳቸው ስለሚመራ ፣ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የመምራት ቀኖናዊ መብት አለው ። ምክንያቱም ቀኖና ያልሻራቸው ፓትርያርክ ፥ ያለ ነውርና ነቀፋ በመንግሥት ኃይል ከመንበራቸው የተሰደዱት አባት ምን ጊዜም ቢሆን የቤተ ክርስቲያን አባት ናቸው ።

**ቅዱስ ሲኖዶስ**
The Holy Synod
4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

Date : 01/17/2013
No. 20 89/2013

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

**ስለ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መከበርና በግፍ የተሰደዱትን ሕጋዊውን ቅዱስ ፓትርያርክ ወደ መንበራቸው ስለመመለስ ከሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ።**

***"እሆ በልዎ ለእግዚአብሔር ወእንብየ በልዎ ለጋኔን፤ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ።" (ያዕቆብ 4፡7)***

ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፤ በ34ኛው መደበኛ ጉባኤ ወቅታዊው የቤተ ክርስቲያኒቱን የሰላምና የእርቅ ሂደት ለማጥናት አስቸኳይ ልዩ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በሎስ አንጀለስ ከተማ እንዲካሄድ መወሰኑ ይታወሳል። በዚህም መሠረት አስቸኳይ የሲኖዶሱ ልዩ ጉባኤ ከጥር 7-9 ቀን 2005 ዓ.ም በሎስ አንጀለስ ከተማ ተካሂዷል።

*መግቢያ*

በእምነቷ፣ በታሪኳና ለትውልድ ባተረፈችው ትውፊቷ በዓለም ጠቢባንና የሃይማኖት ሰዎች ዘንድ የአገራችን ሞገስ እና የልጆችዋ ተስፋ የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን፤ ቀድሞ በጃንደረባው ኋላም በፍሬምናጦስ በተሰበከላት ሕገ ወንጌል ጸንታና በእግዚአብሔር ከንድ ተጠብቃ ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ቆማለች። ሆኖም ይህች ባለታሪክ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ የደረሰችው ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፋ እንደሆነ ሁላችንም የምንረሳው አይደለም። ባለፉት ሃያዎቹ ዓመታት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የደረሰው መከራም ይህን የሚያመለክት ነው። በእነዚህ ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተፈጸመው የሕገ ቤተ ክርስቲያን መፋለስና እርሱንም ተከትሎ የተፈጠረው መከፋፈል፤ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች የልብ ሐዘን ሆኗል። ይህም መከፋፈል ለውጭ ኃይላት ጥቃት፤ ለንብረቶቹዋ መመዝበር፤ ግልጥ ለሆነ የሥነ ምግባር ጉድለትና ሥርዓት አልበኝነት እንድትጋለጥ እንዳደረጋት ልጆቹዋ የሚረዱት ነው።

ይህንንም በቤተ ክርስቲያኒቱ ያንዣበበውን የመለያየትና የመከፋፈል አደጋ በማስወገድ ቤተ ክርስቲያንን በአንድነት ለማገልገል እንዲቻል በገዛ ልጆቹዋ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአንድነትና የሰላም ጉባኤ የእርቅ ጥሪ አቅርቦ በአዲስ አበባ በሚገኙት አባቶችና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በሚመራው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ መካከል የሰላም ድርድር ሲካሄድ መቆየቱ ይታወሳል። ሆኖም ግን ከአዲስ አበባ [illegible] ቤተ ክርስቲያንን አንድነት የማይፈልጉትና፤ ለውጭ ኃይል ዓላማ የቆሙ ጥቂት አባቶች [illegible] አፍነው የሰላሙን ሂደት ፍጹም የሚያጨልም እርምጃ ለመውሰድ ቆርጠው [illegible] እንደሚገልጥ መግለጫ አውጥተዋል። ይህ መግለጫ ከሃይማኖት አባቶች የማይጠበቅ [illegible] ሐሰት የተሞላ ኃላፊነት

1

ግልጽነትና ተጠያቂነት የሌለው መግለጫ ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ እውነቱን እንደገና ለቤተ ክርስቲያኗ ልጆች ለመግለጥ ይገደዳል።

## ሀ. የቅዱስ ፓትርያርኩን መሰደድ በተመለከተ፤

በአዲስ አበባ ያሉት ጥቂት አባቶች የብዙኃኑን ድምጽ በማፈን ባወጡት መግለጫ ላይ፤ « ከሥራው ክብደት የተነሣ ሕመም ካደረብኝ ቆይቶአል ስለሆነም ቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣኑን ተረክቦ ቤተ ክርስቲያንን እንዲመራ» በማለት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንደለቀቁ በማውሳት የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማደናገር ሞክረዋል። ሆኖም ሕዝቡ እንዲያውቀው የሚያስፈልገው

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በፓትርያርክነት የሚመሩት አባት «አሞኛል ሥልጣኔን ተረከቡኝ» ቢሉ እንኳ፤ በኃይል ወደ ፓትርያርክ ምርጫ የተገባው፤ በቤተ ክርስቲያናችን የቀኖና መጽሐፍ በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጽ አንቀጽ 4 ቁጥር 77 « እስከሚድን ጠብቁት» የሚለው ቀኖናዊ ሕግ ተሽሮ ነው።

- የመጀመሪያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በሕመም ምክንያት ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን ለማከናወን ባልቻሉበት ወቅትም በወቅቱ የነበሩት ታላላቆቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በዚሁ ቀኖና ተጠቅመው ለሰባት ዓመታት ያህል ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በእንደራሴ እንድትመራ ያደረጉትና ኋላም ቅዱስ ፓትርያርኩ ሲያርፉ፡ታላቁን ሰማዕት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን በፓትርያርክነት የሾሙት በዚሁ ቀኖና ተጠቅመው ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ ፓትርያርክ « ታመምኩኝ፤ ተረከቡኝ» ብለው ተናግረዋል እየተባለ የሚነገረው ሐሰትና ምንም ማስረጃ የሌለው መሆኑ ይታወቅ ዘንድ አንድም የሰነድ ሆነ የድምጽና የምስል ማስረጃ አልቀረበም፤ የለምም። ይህም ቅዱስ ፓትርያርኩ የተሰደዱት በወታደሮች ተገድደው ከመንበረ ክብራቸው በግፍ እንዲወርዱ እንደተደረገ የሚያረጋግጥ ነው።

የአዲስ አበባዎቹ አባቶች « ቅዱስ ሲኖዶሱን የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠን የቀድሞው ዐራተኛው ፓትርያርክ በራሳቸው እንደበት ሥልጣናችውን እንዲያስረክቡ ያደረገበት ምክንያት የራሱ የሆነ ምሥጢር ይኖረዋል» በማለት በመግለጫቸ አውስተዋል። ምሥጢሩ ምንም እንኳ ለእውነተኞዎቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ግልጥ ቢሆንም እንደገና ልንገልጠው እንገደዳለን።

1. በጊዜው ሥልጣኑን የያዘው መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጋር አንሠራም በማለታቸው፤ ሁኔታው እስኪረጋጋ ድረስ መንግሥትም ማስተዋል እስኪያገኝ ጊዜ ለመስጠት ፤ ነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓም « ሲኖዶሱ ሥራውን እያከናወነ፤ እርሳቸው ጸሎትና ቡራኬ እያደረጉ እንዲቆዩ» በከፍተኛ የመንግሥት ተጽእኖ ተወሰነ።

2. መስከረም 28 ቀን 1984 ዓ. ም ቅዱስ ፓትርያርኩ ያለ አግባብ መንበረ ፓትርያርኩን ለቀው እንዲወጡ በቁጥር 69/298/84 ትእዛዝ ደረሳቸው።

3.ቅዱስ ፓትርያርኩ መስከረም 30 ቀን 1984 ዓ. ም ከመንበረ ፓትርያርኩ በወታደሮች ተገድደው ወጥተው በአዲስ አበባ ከተማ ለአንድ ዓመት ያህል ባልታወቀ ሥፍራ ተቀመጡ።

4.ቅዱስ ፓትርያርኩ ጥር 15 ቀን 1984 ዓ.ም የሽግግሩ መንግሥት ፕሬዚደንት ለነበሩት ለአቶ መለስ ዜናዊ እና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአቶ ታምራት ላይኔ ፤ ለቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና ለጠቅላይ ቤተ

2

ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በጻፉት ደብዳቤ ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን ለማከናወን የሚከለክል እንዳችም የሕመም ችግር እንደሌለባቸውና ሥራቸውንም በሚገባ መሥራት እንደሚችሉ፣ ይህንንም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት እንደሚያውቁት በደብዳቤ ገለጡ።

5. ይህ ሁሉ የቅዱስ ፓትርያርኩ ጥረት ከምንም ሳይቆጠር፣ በማን አለብኝነት ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተጥሶ አባ ጳውሎስ ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓ.ም ላይ በፓትርያርክነት ተሰየሙ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን በኃይል የያዘው አካልም ሕጋዊውን ቅዱስ ፓትርያርክ ስም አጠራራቸውን ለማጥፋት አደጋ ላይ ለመጣል እንጦጦ በሚገኝ መቃብር ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ ስላስገደደ፣ ጉዳዩ ያሳሰባቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች አጅበውዋቸው ቅዱስ ፓትርያርኩ በሞያሌ በኩል ወደ ኬንያ ጥቅምት 1 ቀን 1985 ዓ.ም ተሰደዱ።

6. በጥቅምት ወር 1985 ዓ.ም ሕጋዊው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እርሳቸው እንደሆኑ ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን በራዲዮና በጋዜጣ በይፋ አባታዊ መልእክታቸውን አስተላለፉ ።

7. ከላይ የዘረዘርናቸው እውነታዎች ጊዜው ሲደርስ፣ ዛሬ በሥልጣን ያሉት ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ እና የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ታምራት ላይኔ በአደባባይ እየመሰከሩ ከመሆኑም በላይ፣ በእጃችንም ይህንን የታሪክ እውነት የሚያስረዱ ተጨባጭ ሰነዶች ስላሉ ለሚጠይቀን ማንኛውም አካል ለማሳየት ዝግጁ ነን። ሆኖም ግን በአዲስ አበባ ያሉት ወገኖቻችን ይህን ሁሉ የታሪክ እውነታ ሠርዘው ቅዱስ ፓትርያርኩ « በፈቃዳቸው ጥለውት ሄደዋል» ብለው ያወጡት መግለጫ ፍጹም ሐሰት እና ታሪክን የካደ መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶሱ በአጽንኦት ሊያስገነዝብ ይወዳል።

## <u>ለ. የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስን በስደት መቀጠል በተመለከተ፣</u>

እነዚህ ወገኖቻችን ባወጡት አሳዛኝ መግለጫ ላይ « በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተደርጎ የማይታወቅ በስደት አገር ሲኖዶስ አቋቁመዋል» በማለት ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ምንም ዓይነት ተያያዥነት የሌለው ጥቅስ በመግለጫቸው በመጥቀስ ወቅታዊውን የቤተ ክርስቲያንን እውነት ለመሸፋፈን ሞክረዋል። በተለይም « ያለ ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ አንድ የፋሲካ በዓል ከሀገረ ስብከቱ ውጪ ማክበር በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተከለከለ ነው» በማለትና ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እና ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሲኖዶስ እንዳልመሠረቱ በመናገር ምእመናኑን ለማደናገር ሞክረዋል። በመሠረቱ እነርሱ የጠቀሱት ክፍል ሥርዓትና ሕግ አክባሪ፣ ሰላም አግኝታ ላለች ቤተ ክርስቲያን የሚጠቀስ አንቀጽ እንጂ በባዕድ ኃይል ቅኝ ግዛት ሥር ለወደቀችና ቀኖናዋ ለፈረሰ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቀስ ጥቅስ አይደለም። በስደት ዓለም ሲኖዶስን ስለማቋቋም ከላይ ስለተጠቀሱት ታላላቆቹ ኦርቶዶክሳውያን አባቶችን በተመለከተ፦

1. እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በግፍ የተሰደዱት ብቻቸውን ነው።እንደሚታወቀው አንድ ሊቀ ጳጳስ ብቻውን ሲኖዶስ ሊያቋቁምና ጳጳሳትንም ለመሾም ሥልጣን የለውም። በተለይም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በደታቸው ከግዞት እስር ጋር ስለነበረ፣ ሲኖዶስ ለማቋቋምም ሆነ ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ቀርቶ ለራሳቸው እንኳን ነጻነት አልነበራቸውም። ይልቁንም ዝክረ ታሪካቸው እንደሚያስረዳን ተጋድሎአቸውን ፈጽመው በክብር ያረፉትም በእስር ላይ እንዳሉ ሆነው ነው።

2. ሕጋዊ ቅዱስ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ [illegible] ወንድሞቻቸው ከመንበራቸው በግፍ ወርደው ሲሰደዱ፣ በወቅቱ የምዕራብ ሀገሮች ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ፣ የአውሮፓና የአፍሪካ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኢልያስ፣ [illegible] ፓትርያርኩ እንደራሴ

3

የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ፣ እንዲሁም የቅዱስ ፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስና የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ዲን የነበሩትና አሁን የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ አብረው መሰደዳቸው ታሪክ የሚመሰክረው እውነታ ነው። ይህ በሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ የሚመራ የሊቃነ ጳጳሳት ጉባዔን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ብላ በመሰየም አክብራ ኖራለች ወደፊትም በዚሁ ትቀጥላለች። ይሆን እያወቁ የሲኖዶስን ትርጉም ለማደናገር መሞከር እግዚአብሔርን መዋሸትና ሰፊውንም ሕዝብ በከንቱ ማሳሳት ነው።

ሌላው ደግሞ አባታችን ቅዱስ አትናቴዎስ አምስት ጊዜ ሲሰደድ፣ በእስክንድርያ ያሉት ልጆቹ መንበሩ ባዶ ነው ብለው ሌላ ሰው አላስቀመጡበትም። የቊስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት በኃይል ሌላ ሰው ለማስቀመጥ « አባታችን ነው ብላችሁ ተቀበሉ» ቢላቸው፤ በሃይማኖት ጸንተው ተቃወሙት እንጂ ፈጸምያን ፈቃድ ንጉሥ አልነበሩም ።በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአኩስም የነበሩት አባቶቻችን ከቊስጥንጥንያ የተላከላቸውን በአትናቴዎስ ላይ የተጻፈ ክስ ውድቅ አደረጉት እንጂ አልተቀበሉአቸውም

• ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በሐሰት ሲጋዝ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቹ አባታችንን መልሱልን እያሉ ጮኹ እንጂ ሌላ በአባታቸው መንበር ሲቀመጥ አሜን በለው አልተቀበሉትም። ሲያርፍም ከሳሾች ሳይቀሩ አጽሙን ይዘው « አባታችን ማረን» ብለው አለቀሱ እንጂ፣ የቀድሞው ፓትርያርክ ብለው አልተሳለቁበትም።

ቅዱስ ዲዮስቆሮስም ስደቱን በረከት መከራውን መልእክቱ አድርጎ፤ « ንሥኡ ፍሬ ሃይማኖት፤ የሃይማኖታችሁን ፍሬ እንካችሁ» ብሎ የመከራውን ሲኖዶሳዊ መልእክት ስለላከላቸው፤የመንፈስ ቅዱስ ልጆቹ የአባታቸውን መልእክት ብርሃን አድርገው በሃይማኖት ጸንተው በምግባር ከመትጋታቸውም በላይ ፤ በነገሥታቱ የተሰየመባቸውን መሪ አንቀበልም ብለው፤ የተዋህዶን እምነት አጽንተው ለትውልድ አስተላልፈዋል። በእንጻሩ መለካውያኑ ከቊስጥንጥንያ የተላከላቸውን ይዘው በሌላ መሥመር ተጉዘዋል።

በመሆኑም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የቀደሙትን አባቶቻቸውን እነ ቅዱስ አትናቴዎስን፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅንና ቅዱስ ዲዮስቆሮስን አብነት አድርገው ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን በሰፋት ቀጥለዋል። የአባቶቻቸው አምላክ እግዚአብሔርም ስደታቸውን ባርኮላቸው እነሆ ዛሬ በሕጋዊው ሲኖዶስ ሥር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን በቅንነትና በታላቅ መንፈሳዊ ትጋት የሚያገለግሉ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሹመዋል። ይህም ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋት፣ ለህዝበ ክርስቲያን በሃይማኖት መጽናት እንዲሁም ለመንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት መጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ለተተኪው ትውልድ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖቱንና ኢትዮጵያዊ ታሪኩንና ትውፊቱን ለማስተላለፍ አስችሎአል።

ሐ. የእርቅና የሰላም ውይይቱን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ሕጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስና በአዲስ አበባ የሚገኙትን አባቶች ለማቀራረብ ባቀረበው የሰላምና የእርቅ ጥሪ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አባታዊ ቡራኬና በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ መልካም ፈቃድ የተሰየሙት የሰላም ልዑካን ለሦስት ጊዜ በተካሄደው የሰላም እና የእርቅ ጉባኤ ላይ ተሳትፈዋል። ይህም ጉባኤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የቁርጥ ልጆች ከዳር እስከ ዳር ያነሣሣ ሁሉም ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ተግቶ እንዲሠራ ያደረገ ታሪካዊ ጉባኤ ነው። ከዚህ ጋር ቤትም ጥቂት የማይባሉ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አበው ካህናት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት [illegible] ና የማኅበራት መሪዎች ለሰላሙና ለእርቁ የወሰዱት አስደናቂ አቋም ለሁላችንም ትልቅ ትምህርት ነው።

ሆኖም ግን የአዲስ አበባ አባቶች ባወጡትና እጅግ ሐሰትን በተሞላ መግለጫቸው « መንበሩን እኛ ካልያዝነው ሰላም እና አንድነት ብሎ ነገር የለም» ብሎ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ እንደተናገረ አድርገው ገልጠዋል። የእርቁ ሂደት ምን ይመስል ነበር? ለድርድርስ የቀረበው ሐሳብ ምንን ያካተተ ነው ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ማየቱ ተገቢ ነው።

1. ከአዲስ አበባው ወገን የሰላም ልዑካን የመደራደሪያ ሐሳብ ለማቅረብም ሆነ በሌለውም ከፍል የቀረበውን ለመቀበል እንዳችም መብትና ሲኖዶሳዊ ሥልጣን ሳይሰጣቸው የተላኩ ነበር። ለድርድሩ ያቀረቡትም ከላይ በሰፊው ከነማስረጃው ያቀረብነውን ሐሰት የተሞላበት የእነርሱን አሳብ ፤ ማለትም « ፓትርያርኩ ሥልጣናቸውን የለቀቁት በፈቃዳቸው ስለሆነ ወደ ስድስተኛው ፓትርያርክ ምርጫ እንሂድ» የሚለውን ብቻ ነበር።

2. እንደሚታወቀው በአዲስ አበባ ያሉት ወገኖች አሠራር ሙሉ በሙሉ በገዢው ፓርቲ ትእዛዝና ተጽእኖ ሥር የወደቀ በመሆኑ ፤ የሰላሙን በር የዘጋው ገና የሰላም ጉባኤው ሳይጠናቀቅና ከአዲስ አበባ የተላኩት ልዑካንም ወደአገራቸው ተመልሰው የእርቁ ሰላሙን ሪፖርት ሳያቀርቡ ነበር። ይህም ሊታወቅ በመጨረሻ በዳላስ በተደረገው ጉባኤ ላይ፤ በአንድ በኩል ልዑካንን ልኮ በሌላ በኩል ደግሞ በዐቃቢ መንበሩ አማካይነት በመገናኛ ብዙኀን የተላለፈው አሳፋሪ መልእክት ለእርቀ ሰላሙ ድርድር ምንም በር እንደሌለው በቂ ምስክር ነው።

3. ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተላከው የሰላም ልዑካን ግን በሙሉ ሥልጣን እንዲደራደር ተፈቅዶለት የተላከ በመሆኑ፥ ይህን ከባድ የታሪክ ኃላፊነቱን ለመወጣትና ቤተ ክርስቲያንን አንድ ለማድረግ የበኩሉን ጥረት አድርጎአል። ለዚህም እንደ መደራደሪያ ነጥብ ካቀረባቸው መካከል፤ በታሪክ አጋጣሚ የተከሰተውን የቀኖና ችግር ለማስተካከል እንዲቻል የሁለቱም ፓትርያርኮች መዋዕለ ዘመን እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን በሕይወት ያሉት ፓትርያርክ ወደ መንበራቸው በክብር ተመልሰው መዋዕለ ዘመናቸውን እንዲፈጽሙና እርሳቸውም ሲያልፉ ስድስተኛ ፓትርያርክ ተብሎ በጋራ እንዲሾም የሚል አስታራቂ አሳብ ቀርቦ ነበር። አሁን ግን ከአዲስ አበባ በወጣው የቅሰጣ መግለጫ ላይ « አምስት ብለን አራት አንልም» የሚል የማታለያና የቀጥር ጨዋታ አውጥተዋል።

ይህ ሁሉ የሆነው ለምንድነው ብለን ስንጠይቅ ግን የወያኔ ኢሕአዴግን አመራር ለማስፈጸም በገሀድ የፓርቲው አባላት የሆኑና « እኛ ብንሾምስ?» ብለው ደፋ ቀና የሚሉ ከአምስት ያልበለጡ ጳጳሳት ከመጀመሪያው የሰላሙን ሒደት አምርረው በመቃወማቸው ነው።

እነዚህ ነጥቦች የሚያረጋግጡት ዐቢይ ጉዳይ ቢኖር ቀደም ሲል ለቀኖና ቤተ ክርስቲያን መፋለስ ምክንያት የሆነውና ቅዱስ ፓትርያርኩን በግፍ ከመንበራቸው ያሳደዳቸው ኃይል፤ አሁንም የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ክብር አለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን፤ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማጥፋት ትውልድንም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማዳከም ቆርጦ የተነሣ ኃይል መሆኑን ነው።

በመሆኑም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከላይ በዝርዝር የገለጥናቸውን ዐበይት ጉዳዮች በጥልቀት ከመከረባቸው በኋላ የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና የወደፊት አካሄድን በመመርመርና ቤተ ክርስቲያን ልትጠናከርበት የምትችልበትን ተያያዥ ጉዳዮች በማጥናት የሚከተሉት ውሳኔዎች አስተላልፎአል።

1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ [illegible] ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ናቸው። ይህን እውነት በመሰረዝና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በሚፃረር [illegible] ማናቸውንም የሐዋርያዊ መንበር ሽሚያ ቅዱስ ሲኖዶስ ፍጹም የማይቀበለውና [illegible] ከመሆኑ በላይ በአባቶቻችን ቀኖና መሠረት ድርጊቱን አጥብቆ ያወግዛል።

5

2. ላለፉት ሃያ አንድ ዓመታት በመንግሥት አስተባባሪነትና ደጋፊነት በሕገ ወጥ መንገድ በተቀመጡት አባት ምክንያት ቤተ ክርስቲያናን ከፋኛ የጎዳው መከፋፈል እና መለያየት ሳያንስ፣ አሁን ደግሞ እነዚሀ ጥቂት ጳጳሳት በሥልጣን ያለውን የመንግሥትን ኃይል መከታ አድርገው «ፓትርያርክ» ብለው የሚሰይሙትም፣ አባትነቱ የሐሰት አባት፣ ሹመቱም የሲሞን መሠርይ ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ ያወግዘዋል። በቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደታዘዘው፣ እውነተኞች የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች እስከመጨረሻው ጸንተው በአንድነት እንዲቃወሙት፣ እውቅና እንዳይሰጡትና እንዳይታዘዙት ቅዱስ ሲኖዶስ አስቀድሞ የአደራ መልእክቱን ያስተላልፋል። በተለይም ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ከፍተኛ መሥዋዕትነት በመክፈል የቆሙ እውነተኞቹም አባቶች በዚህ ሒደት ውስጥ ተሳታፊዎች ሆነው በታሪክም በእግዚአብሔርም ተወቃሾች እንዳይሆኑ ጥሪ ያደርጋል።

3. ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሰላምና አንድነት በቆሙትና በኢትዮጵያ እና በውጪው ዓለም በሚገኙት ብፁዓን አባቶች፣ አበው ካህናት፣ ማኅበራትና ሕዝበ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ባለው ወከባ፣ ዛቻ፣ እና ማስፈራራት ቅዱስ ሲኖዶስ በእጅጉ አዝኖአል። በመሠረቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች አሁን እየደረሰባቸው ያለው በደል በአገራችን ባሉት ውድ ዜጎቻችን ላይ እየደረሰ ያለው አጠቃላይ ግፍ አካል ነው። ለተገፉት መከታቸው የሆን እምላክ ግፉን ቆጥሮ ለኢትዮጵያ ትንሣኤን፣ ለቤተ ክርስቲያን ፍጹም ነጻነትን እስኪሰጥ ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያናችን መስቀለኛ መንገድ ላይ ባለችበት በአሁኑ ወቅት፣ ለቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሰላም እንዲሁም ለማኅበረ ካህናትና ምእመናን ኅብረት ይጠቅማል የምትሉትን ሁሉ በጥበብ፣ በማስተዋልና፣ በመንፈሳዊ ጽናት እንድታከናውኑ አደራውን ያስተላልፋል።

4. እጅግ በጣም የሚያሳዝነው፣ ገና ከጅምሩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከም ጠንክሮ እንደሚሠራ ፣ እርሰዋን የሚያዳክምና የሚያጠፉት ሌላ ባእድ ኃይል በምድሪቱ እንዲኖር እንደሚያበረታታ ሰቅዱና ዓላማው አድርጎ የተነሣው አካል፣ እግዚአብሔርን ሳይፈራ፣ ታሪክና ሕዝብንም ሳያፍር « ዓላማችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንንና የአማራን ዘር አከርካሪ መስበር ነው እርሱም ተሳክቶልናል» በማለት በድፍረት ተናግሮአል። ይህ ዓይነቱ አባባል አገርን እንመራለን ሕዝብን እናስተዳድራለን ከሚል ወገን መሰማቱ ቅድስት አገር ኢትዮጵያ በምን ዓይነት አደጋ ውስጥ እንዳለች የሚያመለክት ስለሆነ ኢትዮጵያውያን ሁሉ አገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን ከዚህ አደጋ የምንታደግበትን እግዚአብሔር እንዲያመለክተን ሁላችንም በጸሎት ተግተን እንድንለምነው ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል።

5. ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሕዝቡ ድምጽ እንዲሆን እግዚአብሔር በዘመናችን ያስነሣው ልሳን እንደመሆኑ መጠን፣ ከማናቸውም የዘር፣ የጎሣ እና የፖለቲካ ኃይላት ተጽእና ነጻ በመሆን የሕዝባችን እውነተኛ ድምጽ መሆን እንዳለበት ያምናል። በመሆኑም ሰብእናቸው ተረግጦ የዜግነት መብታቸው ተገፍፎ « የታሪካችን እሻራ የሆነው ታላቁ ገዳማችን ይከበር» በማለታቸው በየእስር ቤቱ ተጥለው ለሚገኙት ገዳማውያን መነኮሳት፣ እንዲሁም መሪር በሆነ እፈናና ረገጣ ውስጥ ስላሉት ጋዜጠኞች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና የፖለቲካ እስረኞች መብት መከበር በመላው ዓለም በተጠናከረ መልኩ አቤቱታውን ለማሰማት ወስኖአል። በተለይም ይህ ሳምንት ኢክርስቲያናዊ ከሆነው ከዘር መድሎ ሕዝባቸውን ነጻ ለማውጣት እስከ መጨረሻው በትዕግሥትና በማስተዋል የታገሉትን አሜሪካዊው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ክቡሩን ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ የሚታሰቡበት ወቅት ነው። በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስ ለእምነታቸውና ለአገራቸው ሰማዕት የሆኑትን የእኛዎቹን አቡነ ጴጥሮስን፣ አቡነ ሚካኤልንና ታላቁን ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስን አብነት በማድረግ፣ በሰደት ዓለም ሆነው ሕዝባችውን በትዕግሥ[illegible]ቲ ቡራኬያቸው እየመሩ ያሉትን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን በመከተል ለሕዝባችን አንድነትና ለቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ለመቆም እግዚአብሔርን እጋዥ [illegible]ሥችአል። እንደሚታወቀው የአገራችን ሕልውና ከቤተ ክርስቲያናችን፣ የቤተ ክርስቲያናችን ሕልውና

6

ደግሞ ከአገራችን ሕልውና ተነጥሎ ስለማይታይ፣ አገር ወዳድ የሆናችሁ ወገኖቻችን ሁሉ ከዳር እስከዳር በመነሣት ከቅዱስ ሲኖዶሱ ጎን በጋራ እንድትቆሙ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

6. ቅዱስ ሲኖዶስ ከላይ የገለጥናቸውን ዓላማዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ መዋቅሩን ይበልጥ አጠናክሮ ለመቀጠል ወስኖአል። በመሆኑም የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት በተጠናከረ መንገድ እንዲደራጅ ፤እንዲሁም ለአርቀ ሰላሙ ሂደት ስኬታማነት በማሰብ ገትቶት የነበረውን አዳዲስ አህጉረ ስብከቶች የማቋቋምና የማጠናከር ሂደት በመቀጠል፣ ለሚቋቋሙት አህጉረ ስብከቶች አዳዲስ ኤጲስ ቆጶሳት ለመሾም ተስማምቷል። ከዚህም ጋር በመላው ዓለም የሚገኘውን የቤተ ክርስቲያኒቱን የዕለት ከዕለት አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚቆጣጠርና የሚያስፈጽም የጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅና ዋና ጸሐፊ ሰይሞአል። የሕዝብ ግንኙነት ክፍልንም አቋቁሞአል። በመሆኑም ለሕጋዊው የቅዱስ ሲኖዶስ መጠናከር የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በጸሎታቸው፣ በእሳባቸው፣ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው አገዛቸውን እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል።

7. ቅዱስ ሲኖዶስ ከዚህ ቀደም የተበተኑትን ለመሰብሰብና የተለያዩትንም አንድ ለማድረግ የተቻለውን ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ነው። አሁንም በበለጠ በልዩ ልዩ ምክንያት የተለያዩትንና ይልቁንም እስከ አሁን የነበረው የልዩነት ችግር ከዛሬ ነገ በሰላማዊ መንገድ በውይይት ይፈታል በማለት በገለልተኛነት የቆዩትን አብያተ ክርስቲያናትና ሌሎች ወገኖቻችንንም በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥላ ሥር በመሆን ለአንዲት አገር፣ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን እና ለአንድ ሕዝብ በጋራ እንድናገለግል ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል። ለቤተ ክርስቲያኒቱ ታላቅ ራዕይና እቅድ ያላችሁ ማኅበራትና የቤተ ክርስቲያኒቱ አቅጣጫ አጅግ ያሳዘናችሁ በአዲስ አበባው አስተዳደር ሥር ያላችሁ አብያተ ክርስቲያናት ለቤተ ክርስቲያናችን ነፃነትና ትንሣኤ በአንድነት እንድንቆም ቅዱስ ሲኖዶስ በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል። ቅዱስ ሲኖዶሱ ይህን የሚያስፈጽም ኮሚቴ ስለሰየመና በመላው ዓለም ተበትነው ባሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች መካከል ለመገናኘትም ዝግጁትን ስላጠናቀቀ፣ ይህን ኮሚቴ በማግኘት ስለቤተ ክርስቲያናችን በጋራ እንድንመካከር ይጋብዛል።

8. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግፍ እና በደል፣ ለዓለም ዓቀፍ የሃይማኖት፣ የሰብአዊ መብትና ማኅበራዊ ድርጅቶች ለማሳወቅ ቅዱስ ሲኖዶሱ ኃላፊነት እንዳለበት ጉባኤው አምኖበታል። ይህን ኃላፊነቱንም ለመወጣት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ከካህናትና ከምእመናን የተውጣጣ ኮሚቴ በማቋቋም፣ በተለያዩ ተቋማት በመገናኘት ግፉን ለመላው ዓለም በይፋ ለማስታወቅ ወስኖአል።

9. ሰሞኑን የቤተ ክርስቲያኒቱን ልጆች ድምጽ በማፈን በአዲስ አበባ በሚገኙ ጥቂት ጳጳሳት የተወሰነው ውሳኔ የብዙዎችን ልብ የሰበረና ተስፋ አስቆራጭ ውሳኔ መሆኑ የታወቀ ነው። ሆኖም ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚያሳስበው ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል እንደሚያልፍ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን በታሪኳ ይህን የመሰለ ብዙ አሳዛኝ ዘመናትን አሳልፋለች፤ በግራኝ አሕመድ አብያተ ክርስቲያናቷ ተቃጥለዋል። ሕዝቦቹዋና ሊቃውንቶቿ ታርደዋል። ቤተ ክርስቲያን ለ15 ዓመታት በመከራ ውስጥ አልፋለች። ሆኖም ይህ ሁሉ ግን አልፎ ዛሬ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በጨለማ ውስጥ እንደ ብርሃን እያበራች ናት። በዚህ አጅግ ፈታኝ በሆነ ወቅትም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተስፋችሁን በእግዚአብሔር ላይ እንድታደርጉ እና በእግዚአብሔር እንድትጽናኑ ቅዱስ ሲኖዶስ መልእክቱን ያስተላልፋል። መንጋውን ለማጽናናት ከመንፈስ ቅዱስ ኃላፊነትን የተቀበለው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ « አጽናኑ ሕዝ[illegible] ኢሳይያስ 40፥1) በሚል መሪ ቃል ዓለም አቀፍ የሰብከተ ወንጌል ሥምሪት ያዘጋጀ[illegible] በሚዘጋጀው በዚህ ጉባኤ ላይ በመገኘት እንድትጽናኑ ቅዱስ ሲኖዶሱ ጥሪውን ያቀርባል።

7

10. ምንም እንኳ ለሦስት ዓመታት ያህል ሲካሄድ የነበረው የእርቀ ሰላም ሂደት ለቤተ ክርስቲያኗ በማያስቡ አካላት ቢሰናከልም፤ በራሱ ተነሣሽነት ላለፉት ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን አንድ ለማድረግ በትዕግሥትና በማስተዋል የዕርቅና የሰላሙን ሂደት ያስተባበረውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና የአንድነት ጉባኤ አባላትን ቅዱስ ሲኖዶስ ከልብ ያመሰግናል።

11. አሁንም ይህን የብዙኀንን ድምጽ በማፈን ሊከናወን የተወሰነው ሕገ ወጥ የፓትርያርክ ምርጫ ተገትቶ ለሰላሙ ቅድሚያ በመስጠት ለሚደረገው ጥረት ሁሉ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በሩን ከፍቶ እጁን ዘርግቶ የሚጠባበቅ መሆኑን እንገልጣለን።

12. በመጨረሻም ይህን ልዩ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በማስተናገድ የደከሙትን የሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም ካቴድራል ካህናት፣ የአስተዳደር ቦርድ እና ምእመናንን ከልብ በማመስገን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቃለ ምዕዳንና ጸሎት ቡራኬ ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤውን አጠናቅቋል።

ጥር 9 ቀን 2005 ዓ. ም

ሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ

8

4127 Redwood Rd.
Oakland CA 94610
(510) 530-3681

No 2098/2013
Date 29.1.2013

Dear Sir/Madam:

Attached you will find a statement of declaration released by the Ethiopian Orthodox Tewhaedo Church-in-Exile based on deliberations at its latest Synodal Meeting held from January 15-18 in Los Angeles, California. The statement discusses in detail the failed peace and reconciliation effort to end the division within the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church (EOTC), why it failed, and who was responsible for the failure. Moreover, the declaration contains several resolutions intended to reach out to all Diaspora EOTCs, including those that have remained neutral for almost two decades, while offering a set of goals that the Exiled Synod seeks to accomplish in the years ahead.

Furthermore, this declaration is intended to provide the facts that truly explain the circumstances leading to the illegal dethronement of His Holiness Abune Merkorios from his patriarchal see, as well as the canonical and practical justifications of establishing a Holy Synod in exile. Above all, the Exiled Holy Synod, via this statement of declaration, wishes to remind that both the clergy and the laity should not recognize the outcome of the pending election of the 6th Patriarch for the EOTC because it would be a serious breach of the longstanding canons and related practices of Oriental Orthodox Churches.

Sincerely,

Abba Melkesedek Workneh, Archbishop and
General Secretary of the Holy Synod-in-Exile

4127 Redwood Rd.
Oakland CA 94610
(510) 530-3681

No 2098/2013
Date 2/12/2013

**"In the name of the Father, and of the Son, and of the Holy Spirit. Amen"**

**Statement of Declaration from the Legal Holy Synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church in Exile on the Upholding of the Church's Cannon Law and the Return of His Holiness Patriarch Abune Merkorios to the Throne from which He was Illegally Ousted**

**"Be subject therefore unto God; but resist the devil, and he will flee from you." (James 4:7)**

***At its 34th biannual conference held in November of 2012 in Columbus, Ohio, the Legal Holy Synod-in-Exile passed a resolution affirming that a special session---a follow-up to the latest peace and reconciliation efforts within the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church--- would be held in Los Angeles. Accordingly, the Synod held the meeting on January 7-9, 2013. Following is the Synod's statement of declaration based on deliberations made at that meeting.***

**Introduction**

The Ethiopian Orthodox Church has remained true to its dogma and practices for centuries. The Church has passed on its legacy from generations to generations, starting first with the evangelism of Eunuch, the treasurer of Queen Candace of Ethiopia, who went to Jerusalem to worship the God of Israel, and later through the missionary work of Abba (Bishop) Fremenatos. Venerated highly by religious scholars and experts throughout the world and regarded as the sources of pride and hope by the Ethiopian Orthodox faithful, the Church has sustained its historic existence for the past two thousand years under the blessings and care of God. However, we are not oblivious to the fact that this highly revered Church has also gone through the rough tumults of history over the years. During the last 20 years, in particular, the Church experienced the worst of this turbulence, when it was seriously challenged with a fundamental breach of canonical law that subsequently led to a division within the Church and a deep sense

of grief among adherents of the faith. The division came from none other than the illegal dethroning of the reigning Patriarch by the regime and replacing him with another. Subsequently, the division further subjected the Church to undue pressure from external forces, while giving way to the looting of its treasures and artifacts, and the improper practices of the faith and of Orthodox dogma.

Mindful of this regrettable blemish on the Church, as well as driven by a genuine concern to save it from continuing turbulence, a few true sons of the Church founded the *Council of Peace and Unity of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church.* The Council resolved to bring the Church back to its normalcy by embarking on a mission that would beget peace and reconciliation between the Holy Synod in Ethiopia and the Legal Holy Synod led by His Holiness Abune Merkorios in North America. Nevertheless, a small group of Archbishops within the Addis Ababa Synod, squashing the voices of the majority membership of that Synod, thwarted the peace and unity mission by announcing a statement that in effect wrecked the chances of bringing about the desired unity of the Church. In its content, not only was the announcement one unexpected of Orthodox Fathers, but also lacked truth, clarity, and integrity of intent; given these facts, therefore, the Exiled Synod has no choice but to issue this statement of declaration to the adherents of the faith in the interest of disclosing the true circumstances that led to the division of our Church and the ramifications thereof.

## A. Concerning the Exile of the Patriarch

The statement issued by a small group of archbishops, after silencing the voices of the majority membership of the Addis Ababa Synod under the pressure of the regime's mighty force, made a bogus claim describing His Holiness Patriarch Markorios's alleged voluntary abdication of his throne in these terms: **"The heavy load of my work has affected my health condition for quite some time and thus I submit that the Holy Synod take over the helm of authority and lead the church."** This false claim, in effect, was a ploy to create confusion among the faithful about the true nature of the Patriarch's removal from the throne. As such, the Orthodox community should be aware of these cardinal facts:

